16ኛ ዓመት ቁጥር 7
16th Year No. 7

ባህር ዳር ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ/ም
Bahir Dar 5th July, 2011

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 14.60
Unit price 14.60

ማውጫ

Content

አዋጅ ቁጥር 179/ 2003 ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ

Proclamation No. 179/2011
The Amhara National Regional State Procurement and Property Administration proclamation

## አዋጅ ቁጥር 179/ 2003 ዓ.ም

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ

የክልሉ መንግሥት ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ሀብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፤

የዕቃዎች እና የአገልግሎቶች ግዥ እንዲሁም የግንባታ ሥራ ከመንግሥት ጠቅላላ ሀብት ከፍተኛውን የወጪ ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ፣

የመንግሥት ግዥ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ከማድረግ በተጨማሪ ሂደቱ ፍትሃዊ፣ ግልጽ እና አድልዎ የሌለበትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ስለሆነ፣

## Proclamation No. 179 /2011

### The Amhara National Regional State Procurement and Property Administration Proclamation

**WHEREAS,** The economic and efficient use of public funds is essential inorder that the Regional Government properly discharge its responsibility;

**WHEREAS,** procurement of goods, works and services constitute a major share of public expenditure;

**WHEREAS,** public procurement must be carried out in a manner which is not only economic and efficient but also fair, transparent and non-discriminatory and shall be accountable;

የመንግሥት ግዥ በክልሉ ለሚከናወኑ የኢኮኖሚ ልማት ተግባሮች መስፋፋት አጋዥ መሣሪያ መሆን ስላለበት፣

ከፍተኛ ሀብት የሚፈስበት የመንግስት ንብረት ለመንግሥት የተሻለ ጥቅም በሚያስገኝ አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውልና አስተዳደሩም ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ የታመነበት ስለሆነ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1 ድንጋጌ መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡-

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "ዕቃ" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሣሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጁ ሶፍት ዌር፣ እንስሳ ሲሆን፣ ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለውን እና ከዕቃዎቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገናና ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት ያለውን ይጨምራል፡፡

**WHEREAS,** public procurement may also be instrumental to the expansion of economic development activities of the Region;

**WHEREAS,** to ensure that public property in which a significant amount of public money is invested, is utilized in such a manner as to enable the government device maximum benefit therefrom and modernize the administration thereof, it is necessary to introduce an intergrated public property administration;

**NOW, THEREFORE,** the Council of the Amhara National Region, in accordance with sub-article 3/1/ of Article 49 of the Revised Constitution of the National Region, hereby proclaimed as follows :

## CHAPTER ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the “Amhara National Regional State procurement and property Administration Proclamation N° 179/2011.”

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1. “Goods” means raw material, products and equipment and commodities in solid, liquid or gaseous form, marketable software and live animals as well as installation, transport, maintenance or similar obligations related to the supply of the goods if their value does not exceed that of the goods themselves;

2. "አገልግሎት " ማለት ከዕቃ፣ ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ሲሆን የጥገና፣ የጥበቃ፣ የፅዳት አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የቄራ እና የውኃ አቅርቦት የመሳሰሉትን ማናቸውም ግዥ ይጨምራል፡፡

3. "የግንባታ ዘርፍ ሥራ" ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፡፡

4. "የምክር አገልግሎት" ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚያከናወኑት የጥናት፣ የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክርም ሆነ፣ ሥልጠና የመስጠት ተግባር ሆኖ በባህሪው የአእምሮ አገልግሎት ነው፡፡

5. "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን እና አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል መሠረት ማግኘት ነው፡፡

6. "መደበኛ ያልሆነ ግዥ" ማለት በዚህ አዋጅ የተገለጹ የግዥ ዘዴዎችን ተከትሎ ግዥ መፈጸም የማያስችሉ ሁኔታዎች ሲገጥሙ ቢሮው በልዩ ሁኔታ መርምሮ ሲያምንበት ውሳኔ የሚሰጥበት የግዥ አፈፃፀም ሂደት ነው ፡፡

2. “Services” means any object of procurement other than works, goods and consultancy services: such as maintenance, security, janitorial, electicity, telecommunication, slaughterhouse and water supply services any procurement;

3. “Construction works” means all works associated with the construction, up grading, demolitiom,repair or renovation of a building road, or structure, as well as services incidental to works, if the value of those services does not exceed that of the works themselves and incluces build-own-operate, build-own-operate transfer and build-operate-transfer contracts;

4. “Consultancy Service” means a service of an intellectual and advisory nature provided by consultants using their profiessional skills to study, design and organize specific projects, advice clients and conduct trainings;

5. “Procurement” means obtaining goods, works, consultancy or other services through purchasing, hiring, or obtainging by any other contractual means;

6. “Informal procurement” means a process of procurement where there exist situations that make the performance of procurement stipulated under this proclamation impossible; and to be executed in a special circumstance where the Bureau believes and decides thereon.

7. "የመንግስት መስሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግሥት መስሪያ ቤት፣ የትምህርት ተቋም ወይም ተመሳሳይ አቋም ያለው አካል ነው፡፡

8. "የመንግሥት ገንዘብ" ማለት ከክልሉ መንግስት ወይም ከከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ግምጃ ቤት ወይም የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስት ካገኘው ድጎማ ወይም የውጭ እርዳታና ብድር ለግዥ ፈፃሚ አካላት የተመደበ ገንዘብ ወይም የግዥ ፈፃሚ አካሉ የውስጥ ገቢ ነው፡፡

9. "የመንግሥት ግዥ" ማለት በግዥ ፈፃሚ አካላት በመንግሥት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው፡፡

10. "አቅራቢ" ማለት ለግዥ ፈፃሚ አካላት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የምክር አገልግሎት ለመስጠት ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ነው፡፡

11. "ዕጩ ተወዳዳሪ" ማለት በመንግሥት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመሳተፍ ያመለከተ ሰው ነው፣

12. "ተጫራች" ማለት የመጫረቻ ሃሣብ ያቀረበ ሰው ነው፡፡

13. "የጨረታ ሠነድ" ማለት ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በግዥ ፈፃሚ አካላትተዘጋጅቶ የሚሰጥ ሠነድ ነው፡፡

14. "የአካባቢ ማስታወቂያ" ማለት በጋዜጣ ፣በሬዲዮና በቴሌቪዥን ለመጠቀም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ቋሚ በሆነ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የሚለጥፉት የግዥ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ነው።

7. "Government Office" means any public body, which is partly or wholly financed by the Regional Government budget, educational institution or a body with similar status;

8. " Public Fund" means any monetary resources appropriated to procuring entities or internal revenue of procuring entities from the Regional Government treasury or from City Administrations and municipalities treasury or subsidy which the Federal Government grants to the Regional Government or from foreign aid and loan;

9. " public procurement" means procurement by a procuring entity using public fund;

10. " Supplier" means a person under contract with a procuring entities to supply goods, give consultancy service or execute works;

11. " candidate" means a person invited to take part in public procurement or seeking to be so invited;

12. " Bidder" means a person submitting a bid;

13. "Bidding Documents" means a document prepared by the procuring entities as a basis for preparation of bids to the bidders;

14. "Local Advertisment" means an invitation to bid (advertisement for procurement) posed on permanent notice board by government offices where it is difficult to serve through News paper, Radio and Television.

15. "የመጫረቻ ሰነድ" ማለት ግዥ ፈፃሚ አካሉ ለግዥው ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መነሻነት ተጫራች በግዥው ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፡፡

16. "ዋጋ" ማለት ለዕቃው፣ለአገልግሎቱ፣ለምክር አገልግሎቱ ወይም ለግንባታ ዘርፍ ሥራው የተሰጠ ዋጋ ሲሆን ይህም ታክስን ጨምሮ ለግዥው የተሞላ ዋጋ ነው።

17. "የግዥ መመሪያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጣ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ነው፡፡

18. " ልዩ ግዥ" ማለት ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በክልሉ መንግሥት ውሳኔ በጥቅል የሚፈጸሙ ከፍተኛ ግዥዎች ወይም የመንግሥት መ/ቤቶች ያላቸውን ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት እንዲሁም አንድ የመንግሥት መ/ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚኖረውን የግዥ ፍላጎት ለማሟላት የሚፈጸም ግዥ ነው፡፡

19. "የማዕቀፍ ግዥ" ማለት ግዥ ፈፃሚ አካላት ያላቸውን ተመሳሳይ የግዥ ፍላጐት እንዲሁም አንድ ግዥ ፈፃሚ አካል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚኖረውን የግዥ ፍላጐት ለማሟላት የሚፈፀም ግዢ ነው፡፡

20. "የማዕቀፍ ስምምነት" ማለት ወደፊት በሚፈጸም ዝርዝር ውል ለሚከናወን አቅርቦት መሠረት በመሆን የሚያገለግል፣ በነጠላ ዋጋ እና በሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተፈጸመ አጠቃላይ የሆነ የግዥ ስምምነት ነው።

15. " Bid proposal" means a document submitted by bidders to participate in a bid on the basis of the bid document prepared by a procuring entity in respect of that procurement;

16. "price" means a price with tax included therein for the procurement of goods, consultancy services or construction works.

17. " Procurement Directive" means the procurement Implementation directive to be issued by the Finance and Economic Development Bureau in accordance with this proclamation;

18. "Special procurement" means a procurement of sizable volume carried out in bulk by a decision of the government of the Region on account of the Regional significance of that procurement or to fulfill similar requirements of various government bodies or requirements of a government body with in a given period of time.

19. "Framework procurement" means a procurement carried out to fulfill similar requirements of various procurement entities or requirements of a procurement entitiy with in a given period of time.

20. "Framework Contract" means a general agreement of procurement establishing unit price and other terms and conditions of contract which serves as a basis for supplies to be delivered under future specific contract.

21. "የመንግስት ንብረት" ማለት ከመንግስት ገንዘብና መሬት በስተቀር የክልሉ መንግስት ሀብት የሆነ ማናቸውም ቋሚና አላቂ ንብረት ነው፡፡ ሆኖም ለከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች መሬት እንደ ንብረት ይቆጠራል።

22. "የንብረት መመሪያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጣ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ነው፡

23. "ቋሚ ንብረት" ማለት ግዙፋዊ ህልወት ያለው፣ የተናጠል ዋጋው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን፣ ከአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚኖረው እንደ የቢሮ ዕቃ፣ ኮምፒውተር፣ ከባድ መሣሪያ፣ ተሽከርካሪ፣ ሕንጻ፣ መንገድ፣ የፍሳሽ መስመር፣ ድልድይ፣ መስኖ እና ግድብ የመሳሰሉትን ይጨምራል::

24. "የሕይወት ዘመን ሥርዓት" ማለት ከመንግሥት ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን የማቀድ፣ የመያዝ፣ የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የፍጆታ ወይም የማስወገድ ወይም ከመዝገብ የመሠረዝ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመንግሥት ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እእንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ነው

25. "አላቂ ዕቃ" ማለት ከቋሚ ዕቃ ውጪ የሆነ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሆን፣ ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል እና ዋጋው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ንብረት ነው::

21. " Public Property" means any fixed asset and suppliesproperty of the Regional Government other than public Fund and land; whereas, land shall be a property for city Administrations and municipalities;

22. "Property Directive" means a property administration directive to be issued by the Bureau in accordance with this proclamation;

23. " Fixed Asset" means tangible asset the value of which is determined by adirective to be issued by the Bureau, that is in operational use and that has a useful economic life of one and more than one year, such as furniture, computers, heavy equipment, vehicles, buildings, roads, sewers, bridges, irrigation systems, dam and the like;

24. " Life-Time Approach" means a system of effective management and control of public property which takes into account all associated activities and costs, namely,planning, acquisition, receipt, use, maintenance, consumption or disposal or deletion of public property;

25. " Supplies" means all public property other than Fixed assets, which can be consumed within one year of use and the value of which is determined by a directive to be issued by the Bureau;

26. “ማስወገድ” ማለት የመንግስት ንብረት በተለያዩ ምክንያቶች ለመ/ቤቱ ተገቢውን አገልገሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ እንደ ንብረቱ ሁኔታ በዝውውር ወይም በሽያጭ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ወይም መቅበር ወይም ማቃጠል ነው፡፡

27. "ቢሮ፣ ዞን፣ ወረዳ እና የቢሮ፣ የዞን፣ የወረዳ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ የዞንና ወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት እና የእነዚሁ ኃላፊ /ሥራ አስኪያጅ ነው፡

28. "ግዥ ፈፃሚ አካል" ማለት ግዥ የሚፈፅምና ንብረትን የሚያስተዳድር የመንግስት መስሪያ ቤት፣ ከተማ አስተዳደርና ማዘጋጃ ቤት ነው።

29. "ከተማ አስተዳደር" ማለት በህግ በታወቀ ወሰን ተደራጅቶ የአንድን ከተማ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር ልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነት በመረከብ የሚመራ የአካባቢ አስተዳደር ነው።

30. "ማዘጋጃ ቤት"ማለት የተሟላ የከተማ አስተዳደር ባልመሰረቱ ከተማ ውስጥ ተጠሪነቱን ለአቅራቢያው ወረዳ ምክር ቤት በማድረግ የተዋቀረ ያልተማከለ የህዝብ አስተዳደር መገለጫና የከተማ ነክ አገልግሎቶችን መስጫ ተቋም ነው።

31. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

26. “Disposal” means the transfer of public property to another person by sale or other means or the act of getting rid of public property by burning or burying when it is found not rendering the appropriate service to the office due to various reasons;

27. “Bureau, Zone, Woreda and the Bureau, Zone and Woreda Head” means Bureau of Finance and Economic Development, Department of Finance and Economic Development and Office of Finance and Economic Development and head or manager of same respectively.

28. “Procuring Entity” means a government body, City administration and municipality that carry out procurement and administer property thereof;

29. “City Administration” means a local administration which, having been organized with in a legally defined border, takes over the political, administrative development and service provision power and responsibility of city residents and directs thereof.

30. “Municipality” means an institution of expression of decenteralized popular administration and one for the provision of urban services organized in a city that has not established a full-fledged local admimistration and is accountable to the surrounding woreda Council.

31. “Person” means natural or juridical person;

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚገኙና ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት በሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም፡-

   ሀ/ ቢሮው አግባብ ካላቸው የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በክልላዊ ደህንነት ጉዳዮች ምክንያት ግዥ በተለየ ዘዴ እንዲፈፀም ዉሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቢሮዉ ግዥዎች በቁጠባና ዉጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችል የግዥ ዘዴ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

   ለ/ ግዥ ፈፃሚ አካላት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ወጭ በመሸፈን ከሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ላይ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ግዥና ንብረት አስተዳደር ላይም ተፈፃሚ ይሆናል።



## 3. Scope of Application

1. This proclamation shall be applicable on the procurement and property administration carried out by offices which are in the Region and fully as well as partially financed by the Regional Government Budget.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article:

   a. The Bureau, in consultation with Heads of the relevant public bodies, may in the interest of Regional Security affairs decide to use various procedures, in which case the Bureaus shall issue a directive to implement the method of procurement enabling procurements to be carried out economically and efficiently.

   b. This proclamation does not apply to contracts procuring entities enter into with another public body for the provision of goods, construction works, consultancy or other services at cost.

3. Without prejudice to sub-article 1 of this Article, this proclamation shall also be applicable on the City Administrations and Municipalities procurement and property administration in the Region.

## 4. የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## 5. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር መርሆዎች

የመንግስት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡-

1. በግዥ አፈፃፀም ረገድ የመንግሥት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማግኘት አለበት ፡፡
2. በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል አድልዎ መደረግ የለበትም፡፡
3. ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ እና ፍትሐዊ መሆን አለበት፡፡
4. ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ናቸዉ፡፡
5. የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ መያዝና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መከታተልና ማረጋገጥ አለበት ፡፡

## 6. ዓለም ዓቀፍ ግዴታዎች

1. ይህ አዋጅ የክልሉ መንግሥት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግሥታት ወይም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ወይም በሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡



## 4. Gender Reference

Provisions of this proclamation set out in mascu line gender shall also apply to the feminine gender.

## 5. Principles of Public Procurement and Property Administration

Public procurement and property administration shall have to comply with the following principles:

1. Ensure value for money in the use of public fund for procurement;
2. Shall not discriminate among candidates on grounds of nationality or any other criteria not having to do with their qualification;
3. Shall be transparent and fairness of the criteria on the basis of which decisions are given in public procurement as well as of decisions in each procurement;
4. Accountable for decisions made and measures taken with regard to public procurement and property administration;
5. Follow up and ensure the careful handling and proper use of public property.

## 6. International obligations

1. To the extent that this proclamation confliclts with an obligation of the Regional Government under or arising out of an agreement with one or more other states or with an international organization, the provisions of that agreement shall prevail.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ስምምነት ለኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ተጫራቾች ልዩ አስተያየት የሚፈቅድ በሚሆንበት ጊዜ የግዥ ፈፃሚ አካሉ ተፈፃሚ የሚሆነው ልዩ አስተያየት በጨረታ ሠነድ ውስጥ በግልጽ እንዲመለከት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 7. የግዥና ንብረት ሠነዶችን ሕዝቡ እንዲያውቅ ስለማድረግ

ይህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጡ የግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎች ሕዝብ እንዲያውቃቸው መደረግ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ በሥርዓት መያዝ አለባቸው።

## 8. የቢሮውና የግዥ ፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### ሀ/ የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

1. በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ መርሆችና አፈፃፀሞች ላይ የግዥ ፈፃሚ አካላት የማማከር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣
2. በክልሉ መንግስት ያለውን የመንግስት ግዥና የንብረት አስተዳደር ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ረቂቅ የህግ ሃሳቦችንና ማሻሻያዎችን ማቅረብ ፣
3. መደበኛ የግዥ ሰነዶችን እና አሠራሩን የሚመሩ ቅፆችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውሉና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
4. የግዥና ንብረት አስተዳደር ጉዳዮችን በሚመለከት ለግዥ ፈፃሚ አካላት የሙያ ፣የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓት መዘርጋትና አፈፃፀሙን መከታተል፣



2. Where an agreement referred to in sub-article 1 of this Article contains a preference or preferences in favour of national and resident bidders, the procuring entity shall ensure that the applicable preference or preferences are clearly stated in the bidding documents.

## 7. Public Accessibility of legal Documents

This proclamation and the procurement and property administration directives to be issued by the bureau pursuant to this proclamation shall be made accessible to the public and systematically maintained for use.

## 8. Duty and Responsibility of the Bureau and the Procuring Entities

### A/ Duty and responsibility of the Bureau

1. Provide for an advisory service and technical support to the procuring entities on public procurement and property administration policies, principles and implementation;
2. Deliver the draft of legal issues and amendments of the public body procurement and property administration to be effective throughout the Regional Government;
3. Prepare, update and issue authorized versions of the standard bidding documents and procedural forms;
4. In accordance with procurement and property administration, introduce the profession, working and organizational procedure to procuring entities and follow up its implementation;

5. ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች፣ ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶችና ቅፆች ወይም ከተፈቀዱ የንብረት አወጋገድ ሥርዓቶችና ስልቶች ውጪ በግዥ ፈፃሚ አካላት ግዥ ለመፈፀም ወይም ንብረት ለማስወገድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፣

6. በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው አቅራቢዎች የሚመዘገቡበትን የተቀላጠፈ ሥርዓት መዘርጋት፣በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣መርምሮ መመዝገብ እና የምዝገባውን ዝርዝር ማሰራጨት፣

7. በዕጩ ተወዳዳሪዎችና በአቅራቢዎች ላይ የግዥ ፈፃሚ አካላት የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔ ቅጅዎች ለሚመለከታቸው ማሰራጨት፣

8. ከግዥ ፈፃሚ አካላት ጋር ባደረጉት የግዥ ውል መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው፣ ስለብቃታቸው ሃሰተኛ ማስረጃ በማቅረባቸው ወይም በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ባለመፈፀማቸው ቢሮው በመንግስት ግዥ አፈፃፀም እንዳይሳተፉ ያግዳል፡፡ እንዲሁም ያገዳቸውን አቅራቢዎች ዝርዝር መያዝና ማሰራጨት፣

9. የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ተግባራትን፣ ይህንን አዋጅ እና ሌሎች የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር የሚመራባቸውን ሰነዶችን ጠብቀው የተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥና ንብረት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

5. Consider and decide on request from procuring entities to deviate from the prescribed methods of procurement, the standard bidding documents and procedural forms in effecting procurement or use other systems or methods of disposing of public property than those authorized by law;

6. Introduce an efficient system of listing under which suppliers who are interested to participate in public procurement are registered; receives, reviews, and records applications by candidates for registered supplier status and distribute the suppliers list;

7. Review and decide on complaints submitted by procuring entities on the conduct of bidders or suppliers, and send copies of such decision to the concerned organs;

8. Maintains and distributes a list of suppliers who by reason of having seriously neglected their obligations under a public procurement contract, or having provided false evidence about their qualifications or not performing duties stipulated in this proclamation have been debarred from participating in public procurment by the Bureau;

9. Conduct follow up and supervision to ensure that procurement and property administration activities of public bodies are in accordance with this proclamation and other documents governing public procurement and property administration;

10. ለግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር የሚያገለግል የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፣
11. ስለ መንግስት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር ጥናት እና ልዩ ልዩ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ማካሄድ፣
12. ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣

## ለ/ የግዥ ፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ስለሚያከናውኑት ግዥ እና ስለውሉ አፈፃፀም ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል ፡-
   - ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በተገለፀው መሠረት በወቅቱ የግዥ ዕቅድ አዘጋጅቶ የማፀደቅ፣
   - ለ/ የጨረታ ማስታወቂያዎችን ማውጣት፣ የተጫራቾችን ዝርዝር ውጤቶችንና አሸናፊዎችን የማሣወቅ፣
   - ሐ/ የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ፣ አሸናፊውን ከማስታወቅና ውል ከመፈረሙ በፊት በቂ በጀት መኖሩን የማረጋገጥ፣
   - መ/ የግዥ ውሎችን መፈረም ፣
   - ሠ/ በተጫራቾች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሣኔ የመስጠት፣

10. Put in place a system useful for the handling and implementation of information of procurement and property administration; thereby deliver same in time to the concerned bodies.
11. Conduct study and various capacity building activities on public procurement and property administration;
12. Folow up and ensure the implementation of this proclamation as well as regulations and directives to be issued in accordance with this proclamation.

## B/ Duty and Responsibility of the Procuring Entities

1. Procuring entities shall have responsibility for their act of procurement and contractual performance; and particularly they shall have the following duties:
   - a. Prepare and cause to be approved timely the procurement plan in accordance with Article 10 of this proclamation;
   - b. Issue invitation to bid; and notify the detailed results of bidders and winning bidders;
   - c. Ensure the availability of adequate budget for procurement activity before issuing bid invitations, notifying bid winners and signing a contract;
   - d. Singn contracts for procurement
   - e. Investigate and thereby render a decision on complaints lodged by bidders;

ረ/ የአቤቱታዎችን ቅጅ የምርመራ ግኝቶችን እና በግኝቶቹ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ የያዘ ሪፖርት ለቢሮው እና በየደረጃው ላሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያና ጽህፈት ቤቶች እንዲሁም ለከንቲባ ጽህፈት ቤት ማቅረብ፣

ሰ/ ከአሸናፊው ጋር የተደረገው ውል፣ አሸናፊ በሆነባቸው ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት መፈፀሙን የማረጋገጥ፣

ሸ/ እንደአስፈላጊነቱ የግዥ ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ ሦስተኛ ወገኖችን የመቅጠር፣

ቀ/ የመንግስት ግዥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እና በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ፣

በ/ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ስነ-ምግባርን ማክበር፣

ተ/ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ይህን አዋጅን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ ማረጋገጥ፣

ቸ/ ስለ ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መከተልና በተጠየቁበት ጊዜ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

2. በየደረጃው ያሉ ግዥ ፈፃሚ አካላት የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደቶች እንዲሁም ከመሥሪያ ቤቶች የሥራ ባህሪ አኳያ ታይቶ ግዥን በእራሳቸው እንዲፈጽሙ የተፈቀደላቸው ሌሎች የሥራ ሂደቶች ግዥን የማቀድ፣ የመወሰንና የመተግበር ኃላፊነት ተሰጥቷል፡፡

f. Submit a copy of any complaints, investigation findings and reports of the findings and decisions to the bureau,various level economic and development department and offices and Mayor Office;

g. Ensure that the implementation of the awarded contract is in accordance with the terms and conditions of the award;

h. Employ third parties who cause the execution of procurement activities as deemed necessary;

i. Ensure public procurement shall be based on the plan and maintain procurement principles in accordance with this proclamation;

j. Respect the ethics of public procurement and property administration;

k. Ensure public procurement and property administration shall be based on this proclamation;

l. Follow the modernized information maintaining procedure and have obligation to deliver in accordance with procurement implementation and property administration.

2. Procuring entities in different levels, procurement, finance and property administratraion supporting processes and other business processes, those are permitted to execute procurement by themselves according to the organizations behave, shall be given to plan procurement, make a decision and execution responsibility.

3. የግዥ ፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች እና ለግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ የተመደቡ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሰረት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

4. የግዥ ፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች እና ግዥና ንብረት አስተዳደር የተመደቡ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በቁጥጥራቸው ሥር የሚገኘን ማንኛውንም የመንግስት ሀብትና ንብረት ውጤታማ በሆነ መንገድ እና ለታለመለት ዓላማ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን ማረጋገጥ እና ችግሮች ቢከሰቱ ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

## 9. የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥነ-ምግባር

1.በግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች የሚከተሉትን የስነ-ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ማከናወን አለባቸው፡-

ሀ/ የተፈጠረ ወይንም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን የማሳወቅና ራስን ከሒደቱ የማግለል፣

ለ/ ለዕጩ ተወዳዳሪዎችና አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና የመፈፀም እድል የመስጠት፣

ሐ/ በሥራ አጋጣሚ ያወቋቸውን የግዥ ፈፃሚ አካላት እና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ወይም የአቅራቢዎችን መረጃ በሚስጥር መጠበቅ፣

መ/ ስጦታ ወይም የሥራ ዕድል ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

3. Heads of procuring entities and the classified heads and personel to the procurement and property administration, shall be accountable for their actions in accordance with this proclamation.

4. Heads of procuring entities, and the classified heads and employees of procurement, shall ensure any public property under them held with effective and intended objective, and take conditional corrective measures if problems arise.

## 9. Rules of Ethics in Public Procurement and Property Administration

1. personel engaged in public procurement and property administration shall have to observe the following rules of ethics in the discharge of their duties:

a. the obligations to notify any actual or possible conflict of interest and isolate oneself from any processes involving such conflict;

b. to give candidates and suppliers equal opportunity of competition and performance;

c. keep in secret any confidential information concerning procuring entities, candidates or suppliers which he/she came to know on account of his/her duty;

d. to reject any gift or offer of an employment opportunity or anything of monetary value or service;

ሠ/ በስራ ሒደት ያወቋቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይንም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈፃሚ አካላት የማሳወቅ እና ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ፣

ረ/ ለሕዝብ ሐብትና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን፣

ሰ/ የተሰጣቸውን ኃላፊነት የአገልጋይነት መንፈስ በመያዝና በቁርጠኝነት መወጣት።

2. ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የመንግስት የግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድን ሊያዛባ ከሚችል ከማንኛውም ተግባር ራሱን ማግለል አለበት፣ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 13 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ/ የግዥ ፈፃሚ አካል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሣኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ጋር በተያያዘ ግዥ ፈፃሚ አካሉ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ አለመስጠት ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል አለመግባት ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመስጠት፣

ለ/ የመንግስት ግዥ አፈፃፀምን ወይንም ንብረት አወጋገድ ለማዛባት በማሰብ የሐሰት ማስረጃ አለማቅረብ ወይንም መግለፅ የነበረበትን መረጃ አለመደበቅ፣

ሐ/ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሐሰት ውድድር አለማድረግ፣

e. to report to the law enforcement agencies any intended or completed action of corruption and contribute to the effort to fight corruption and malpractice;

f. demonstrate concern to public resource and property;

g. fulfill their responsibility by withholding service spirit and courageously.

2. Any candidate or supplier shall have to refrain from any act contravening the process of public procurement and property disposal. Without prejudice the provisions of chapter thirteen of this proclamation, any candidate or supplier shall have the responsibility:

a. with an interntion to influence the decision or action of the head of procuring entity or personel persuade the procuring entity to change its established practice of procurement and property disposal, not to give directly or indirectly gifts of any kind in the form of inducement, not to promise to give gifts, not to offer employment opportunity or anything of monetary value or service;

b. with an intention to mislead a procurement proceeding not to present a falsified document or not to withhold information he/she should have disclosed;

c. not to connive with another candidate in an act of false competition in order to get unfair advantages;

መ/ በስራ ሒደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይንም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈፃሚ አካላት የማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች

### 10. የግዥ ዕቅድ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በበጀት ዓመቱ የሚፈጽሙትን ግዥ ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተና በምክንያት የተደገፈ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በጀት በፀደቀ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት የተዘጋጀው ዕቅድ የግዥ ተግባርን ለሚፈፅሙ የሥራ ሂደቶች ማቅረብ ወይም መላክ ይኖርባቸዋል።
3. ግዥ ፈፃሚ አካላት የግዥ ዕቅድ ሲያዘጋጁ የግዥ ፍላጎትን የመለየትና የማደራጀት፣ የግዥ ዘዴን የመምረጥ፣ የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን የመወሰን እና የግዥ ዕቅድ የሚሻሻልበትንና የሚፀድቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው።

### 11. የግዥ ሠነዶች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከመንግሥት ግዥ ጋር የተያያዙ መዝገቦች እና ሠነዶችን ግዥው ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ እስከ ሚገለጸው ጊዜ ድረስ ማቆየት አለባቸው፡፡ በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

d. to report to the law enforcement agencies any intended or completed action of corruption which he came to know during the procurement proceedings and contribute to the effort to fight corruption and malpractice;

## CHAPTER TWO

## BASIC PROCUREMENT PROVISIONS

### 10. Procurement plan

1. Procuring entity shall have to prepare an annual procurement plan showing their procurement for the concerned budget year and containing such details with in 30 days after the budget approved.
2. The prepared plan in accordance with sub-article (1) of this Article, shall have to be presented or sent to the business processes those who execute procurement activities.
3. Procuring entities, when prepared the procurement plan, identify and organize the procurement needs, select the method of procurement, decide the time of procurement and shall have a responsibility to make suitable condition of revision and approvement.

### 11. Procurement Documents

1. Procuring entities shall have to maintain records and documents regarding public procurement for such period of time as is determined by the directive to be issued by the Bureau from the date of concluding any procurement proceeding, such informations shall include the following:

ሀ/ የሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎችን ወይም አገልግሎቶችን አጭር መግለጫ፣

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ የሰጡ አቅራቢዎች ወይም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ፣

መ/ ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ፣የጨረታ ግምገማ የውድድሩን አፈፃፀም፣ ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሣብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

ሠ/ በቀረበው አቤቱታ መሠረት ጨረታውን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ውሣኔ የተሰጠበትን አካሄድ የሚያሳይ መረጃ፣

ረ/ ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ሥርዓቶችን መከተል የተመረጠበትን ምክንያት፡፡

2. የግዥው ሂደት ተጠናቆ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታው ዕጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልታዘዘ እና በፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካሉ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፡፡

ሀ/ የተጠየቀው መረጃ ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣ የሕግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጐዳ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

a. A brief description of the goods, works or services to be procured;

b. The invitation to bid;

c. The names and addresses of suppliers that submitted bids proposals or the names and addresses of the winning bidders;

d. The evaluation criteria stipulated and applied and a summary of the evaluation and comparison of bids, proposals and quotations received;

e. Information on any decision to suspend or cancel proceedings after having been initiated; and

f. The grounds for using a procurement procedure other than open bidding.

2. The record concerning any proceeding shall on request, and once the proceedings have resulted in a contract or have otherwise been terminated, be made available to candidates who participated in the proceedings. However, except when order to do so by a competent court and subject to the conditions of such an order, the procuring entity shall not disclose:

a. Information requested if its disclosure would be contrary to law, would impede law enforcement, would not be in the public interest, would prejudice legitimate commercial interest of the parties or would inhibit fair competition;

ለ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ /መ/ ሥር በተመለከተው መሠረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሠነድ ካልሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሣብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ እና ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የመወዳደሪያ ሃሣቦች እና የጨረታ ሠነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች፡፡

b. Information relating to the examination and evaluation of bids proposals or quotations and the actual content of bids, proposals or quotations other than in the summary form referred to in sub-article 1(d) of this Article.

## 12. አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 የተደነገገው ልዩ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት ግዥ ተሳታፊ እንዳይሆን ሊደረግ አይችልም፡፡

## 12. Impartiality

Without prejudice to Article 13 of this proclamation, candidates shall not be excluded from participation public procurement on the basis of nationality, race or any other criterion not having to do with their qualifications.

## 13. ልዩ አስተያየት

1. በጨረታ ግምገማ ወቅት በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እና በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ከሚከናወኑ የምክር አገልግሎት ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡
2. የዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ እኩል ነጥብ ሲያገኙ ለአገር ውስጥ ምርቶች፣አገልግሎቶች ወይም ኩባንያዎች ቅድሚያ ይሠጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም ማናቸውም ዕቃ ከዋጋው ከ35% በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል፡፡

## 13. Preference

1. A preference margin shall be done for goods produced in Ethiopia, for works carried out by Ethiopian nationals and for consultancy services rendered by Ethiopian nationals be granted in the evaluation process.
2. Where in the evaluation of bids for procurement of goods, services or works equal percentage points are resulted for bidders offering similar price and quality, preference shall be given to local goods, services or companies.
3. For the purpose of sub-article (1) of this Article, any good to which more than 35% of the value added occurs in Ethiopia shall be deemed as one which is produced in Ethiopia.

4. በግዥ አፈፃፀም ረገድ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ተቋማትን ለማበረታታት የሚያስችል ልዩ አስተያየት ሊደረግ ይችላል:: ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## 14. የግንኙነት ስልት

1. በግዥ ፈፃሚ አካላት እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በጽሁፍ መደረግ አለባቸው፡፡ በጽሁፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች ወዲያውኑ በጽሁፍ መረጋገጥ አለባቸው፡
2. ግዥ ፈፃሚ አካላት የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት በምስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጡ ከጽሁፍ በተጨማሪ ወይም በጽሁፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ፡፡

## 15. ቋንቋ

1. ዓለም አቀፍ ተጫራቾች የሚሳተፉበት ግዢ ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት ብሔራዊ የጨረታ ሰነድ የሚዘጋጀውና ጨረታው የሚካሔደው በአማርኛ ቋንቋ ነው። ሆኖም ለግዥው አካሔድ አመቺ መሆኑ ከታመነበት የተሟላ ውድድርን እንደማይገድብ ተረጋግጦ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ለሚሳተፉበት የአገር ውስጥ ጨረታ፣ የጨረታ ሰነድ እእና የመጫረቻው ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲዘጋጁ ግዥ ፈፃሚ አካሉ ሊፈቅድ ይችላል።

4. There shall be made a preference with a view to encouraging micro and shall trade and industry institutions with regard to procurement execution. Particulars shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

## 14. Form of communications

1. Communications between candidates and procuring entities shall be in writing. Any communication not made in written form shall be immediately referred to and confirmed in writing.
2. Subject to necessary safeguards with regard to authenticity and confidentiality, and when thechnical conditions so permit, the procuring entities may determine the extent by which communication by electronic means may be used in addition to or instead of writing.

## 15. Language

1. Except where a procurement proceeding involves international bidders, for national bids in which only local bidders participate, the bid documents shall be prepared and the bid process shall be conducted in the Amharic language. However, if it is found to facilitate the procurement process, the procuring entity concerned may authorize the use of English language in the preparation of bid documents and bid proposals in a national bid in which only local bidders participate, provided that such an act is not prejudicial to fair competition.

2. ለዓለም አቀፍ ግዥ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጁት ማናቸውም ሰነዶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን ይኖርባቸዋል።

## 16. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

1. በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ግዥ ፈፃሚ አካላት ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡

ሀ/ በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ እና ሌሎች የመገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ዝግጁነት ፣

ለ/ ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ፣

ሐ/ በእዳ ያልተያዙ፣ ያልከሠሩ ወይም የሥራ እንቅስቃሴን ያላቋረጡ፣ ከንግድ ሥራ ያልታገዱ፣

መ/ የታደሰ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ያላቸውና በአገሪቱና በክልሉ የግብር ሕግ በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታን የተወጡ ሆኖ መገኘት፣

ሠ/ በግብር ከፋይነት ተመዝግበው መገኘትና የተመዘገበ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጣቸው፣

ረ/ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ ፡፡

2. ግዥ ፈፃሚ አካሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሠነድና ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

2. For procurement to be conducted by means of international competitive bidding, all documents shall have to be prepared in English Language.

## 16. Qualification of candidates

1. In order to participate in public procurement, candidates must qualify by meeting the following criteria and such other criteria, as the procuring entities consider appropriate under the cirocumstances:

a/ That they possess the necessary professional and technical qualifications and competence, financial resources, equipment and other physical facilities, managerial capability, experience in the procurement object, reputation, and the personnel, to perform the contract;

b/ That they have the legal capacity to enter into the contract;

c/ That they are not bunkrapt or wound up,their business activities have not been suspended;

d/ That they have renewed trade or job license and fulfilled their obligations to pay taxes according to the Nation and Regional state tax laws;

e/ That they have registered as tax payers and possessed tax payer’s identification number;

f/ That they are registered in the suppliers list.

2. The procuring entity may require candidates to provide such appropriate documents and other data as it may deem useful to satisfy itself that the candidates are qualified in accordance with the criteria referred to in sub-article 1 of this Article.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሠነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሃሣብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሠነዶች ውስጥ መመልከት ያለባቸው ሲሆን፣ በሁሉም ተጫራቾች ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት የሚቀርቡትን ሠነዶች እና የመመዘኛ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብቃት መገምገም አለባቸው፡፡

5. ግዥ ፈፃሚ አካላት ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሀሰተኛ መረጃ የያዙ ሠነዶችን ያቀረቡ ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ያልተሟላ መሆኑ በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠባቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጭ እንዲሆኑ ለመወሰን ይችላል፡፡

## 17. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

1. ስለግዥው ምንነት ፣ ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚገዙዋቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህርይ የሚያሳይ የቴክኒክ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

3. Any requirement established pursuant to sub-article 1 of this Article shall be set forth in the bid documents or other documents for solicitation of proposals, and shall apply equally to all candidates.

4. The procuring entities shall evaluate the qualifications of candidates based on the presented documents and the evaluating criteria set forth as submitted to it pursuant to sub-articles 1 and 2 of this Article.

5. The procuring entities may disqualify a candidate who submits document containg false information or the presented document for the purpose of qualification is significantly erroneous, or the document is confirmed at any time that it is incomplete.

## 17. Technical Spesification

1. Technical specifications and descriptions laying down the characteristics of the goods, works or services to be procured shall be prepared for the purpose of providing a correct and complete description of the object of procurement and for the purpose of creating conditions of fair and open competition between all candidates,

2. የቴክኒክ መግለጫው የግዥ ፈፃሚ አካላትን ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት ጠቀሜታ፣ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን፣ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆነውን ባህሪ የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

3. በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚዘጋጀው የቴክኒክ ዝርዝር መግለጫ አግባብነት እስካለው ድረስ፣

ሀ/ በዲዛይን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣

ለ/ አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ሐ/ ሰፊ ውድድርን የሚጋብዝና ውድድርን ሊገድቡ የሚችሉ መግለጫዎች ያልተካተቱበት መሆን አለበት።

4. የግዥ ፈፃሚውን አካል ፍላጐት በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚጠቅስ መሆን የለበትም፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ "ወይም ተመሳሳዩን" የሚል ሀረግ በዕቃ ወይም አገልግሎት ዝርዝሩ ውስጥ መታከል ይኖርበታል።

2. The technical specifications shall clearly describe the procuring entities requirements with respect to quality, performance, not harmful, safety and where necessary dimensions, symbols, terminology, packaging, marking and labeling or the processes and methods of production and requirements, relating to conformity assessment procedures,

3. Technical specification prescribed by procuring entities shall, as far as possible:

a. Be interms of performance rather than design or descriptive lonely characteristics;

b. Be based on national standards, where such exist, or otherwise on internationally recognized standards or building codes;

c. Inviting open competition and devoid of any statement having the effect of restricting competition.

4. There shall be no requirement or reference in the technical specifications to a particular trademark or name, patent, design or type, specific original producer or service provider, unless there is no sufficiently precise or intelligible way of describing the procurement requirements of the procuring entity and provided that words such as "or equivalent" are included in the specifications.

## 18. ጨረታንና የመወዳደሪያ ሃሣብን ውድቅ ስለማድረግ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከሚከተሉት በአንዱ ወይንም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ሀ/ በግዥ አካሔዱ ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈፀሙ ከተረጋገጠ፣

ለ/ በሥራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም የግዥ ፈፃሚ አካላትን ፍላጐት ለማሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ግዥውን ማካሔድ ለግዥ ፈፃሚ አካላቱ የተሻለ ቴክኒካል ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን፣

መ/ በጨረታ የቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ በላይ ሲሆን፣ እና ግዥ ፈፃሚ አካሉ ድጋሚ ጨረታ በማውጣት የተሻለ ዋጋ የሚገኝ መሆኑን ሲገምት፣

ሠ/ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ በግዥ ፈፃሚ አካላት ለግዥው ከተያዘው በጀት በላይ ሲሆን እና የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይችል ሲሆን፣

ረ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የግዥ አካሔዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፡፡

## 18. Rejection of Bids and proposals

1. Procuring entities may for one or more of the following reasons reject in whole or in part bids and proposals at any time prior to the conclusion of procurement contract where:

d. There is proof of error in the procurement proceeding which could affect the outcome of the bid;

e. It is ascertained that the procurement has no use in enabling the procuring entities to obtain a better technical or economic advantage as a result of a change of work plan or another alternative representing a better option to meet the requirement of the procuring entities;

f. Bidders fail to meet the minimum criteria set forth in the bid document;

g. The minimum price offered in the bid does not match with the timely market price and the procuring entity expected that it can get a better price acvantage by re-advertising the bid;

h. The price offered by the successful bidder exceeds the budgetary allocation made for the procurement and the procuring entity can not make up for the deficiency from any other source;

i. It is proved that the bidding is not sufficiently competitive as a result of connivance among candidates.

2. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረታውንና የመወዳደሪያ ሀሳብን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ሲሰርዙ ምክንያቱን የሚገልፅ ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪ- ዎች ወዲያውኑ እንዲደርስ ማድረግ አለባቸው። ሆኖም የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ አይገደዱም::

3. ጨረታውን ውድቅ የማድረጉ ውሣኔ የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ እንደታሸጉ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው::

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረታንና የመወዳደሪያ ሀሳብን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም::

## 19. የጨረታ ዋጋና የዋጋ ማስተካከያ

ቢሮው ግዥ ፈፃሚ አካላት ለግንባታ ሥራዎችና በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸሙ ግዥዎች የጨረታ ዋጋና የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ዝርዝሩም ቢሮው በሚያወጣው የአፈፃፀም መመሪያ ይገለፃል።

## 20. የግዥ ዘዴዎች

1. በመንግስት ግዥ አፈፃፀም የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ/ ግልፅ ጨረታ ፣

ለ/ ውስን ጨረታ ፣

ሐ/ በዋጋ ማቅረቢያ (በፕሮፎርማ) የሚፈፀም ግዥ፣

መ/ በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ፣

ሠ/ በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣

ረ/ የሁለት ደረጃ ጨረታ ናቸው።

2. Procuring entities shall have to give notice to candidates forth with disclosing the reasons for rejecting bids and proposals wholly or partially in accordance with sub-article (1) of this Article. However, they shall not be required to justify the reasons.

3. If the decision to reject all bids results before the opening date and time, the bids received shall be returned unopened to the candidates submitting them.

4. The procuring entities shall icur no liability towards candidates solely by virtue of its invoking sub-article (1) of this Article.

## 19. Values of Bids and values Modification

Bureau allows for the works and framework cantract procurement values of bids and values modification by procuring entities. The particulars shall be specified with issued implementation derectives by the Bureau.

## 20. Methods of procurement

1. The following methods shall be used in public procurement:

a/ Open Bidding;

b/ Restricted Tendering;

c/ Request for quotation (proforma);

d/ Direct procurement;

e/ Request for proposals;

f/ Two stage Tendering

2. በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡

3. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በዚህ አዋጅ የተገለፁት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ይሆናል፡፡

4. ግዥው ወጭ ቆጣቢ፣ግልፅና ዘመናዊ እንዲሆን የሚያስችል ለማድረግና ግዥ ፈፃሚ አካላትና የአቅራቢዎች አሰራርና አቅም በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ ለመፈፀም ቢሮው ዝግጁ በሆነ ጊዜ ተገቢውን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ሥርዓቱ በተወሰኑ ወይም በሁሉም የመንግስት ግዥዎች ተፈፃሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

## ምዕራፍ ሦስት

## ግልጽ ጨረታ

### 21. የጨረታ ማስታወቂያ

1. የጨረታ ማስታወቂያ አገራዊ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ክልላዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ላይ መውጣትና ከተቻለ ደግሞ በሬድዮና በቴሌቪዥን ጭምር መገለጽ አለበት፡፡
2. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ዉስጥ ካስቀመጠዉ አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

2. Except as otherwise provided in this proclamation, procuring entities shall use open bidding as the preferred procedure of procurement.

3. Procuring entities may use a method other than open bidding only where conditions for use of such other method stipulated under this proclamation are satisfied.

4. to make the procurement cost effective, transparent and modernized the system and the capacity of procuring entities and suppliers allows the carrying out of procurement through electronic exchange of information, the Bureau may authorize the implementation of the electronic system in all or certain public procurement proceedings by establishing the appropriate framework for the operation of the proposed electronic system.

## CHAPTER THREE

## OPEN TENDERING

### 21. Advertisements

1. Invitation to bid shall be advertised in a national or regional news paper, and if possible the bid shall also be noticed in radio and television.
2. The time allowed for candidates to submit bids shall not be less than a minimum number of days to be stated in a directive to be issued for the implementation of this proclamation.

3. የአካባቢ ማስታወቂያ መጠቀም ቢፈለግ በቂ አቅራቢዎች እንደሚገኙ ሲታመንበት እና በመመሪያው በሚገለፀው የገንዘብ መጠን መሠረት በአካባቢያቸው የሚገኙ አቅራቢዎችን ተጠቅመው ግዥ መፈፀም እንዲችሉ የአካባቢ ማስታወቂያ መጠቀም ይችላሉ።

## 22. የጨረታ ጥሪ

የጨረታ ጥሪ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

1. የግዥ ፈፃሚውን አካል ሙሉ ስምና አድራሻ፣
2. ዕቃው መቅረብ ወይም ሥራው መጠናቀቅ ያለበትን ጊዜ ጨምሮ የዕቃውን፣ የግንባታ ሥራውን እና የአገልግሎቱን አጭር መግለጫ፣
3. የጨረታውን ሠነድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እና የጨረታ ሠነዱ የሚገኝበትን ቦታ፣
4. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ የሚቀርብበትን ቦታ እና የማቅረቢያውን የመጨረሻ ጊዜ፣
5. ጨረታው የሚከፈትበት ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ተጫራቾች ወይም ተወካዮች ጨረታው ሲከፈት መገኘት የሚችሉ መሆኑን በራሳቸው ፈቃድ ባይገኙ ግን ጨረታውን ከመክፈት የማይታገድ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፣
6. ግዥ ፈፃሚ አካሉ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ።

## 23. የጨረታ ሠነድ

1. በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላ፣ ገለልተኛና ተጨባጭ መሠረት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የጨረታው ሠነድ በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት፡፡ በተለይም ሠነዱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡-

3. It is possible to use local advertisements and execute procurement locally if believed there is a sufficient local supplier and with the amount of money specified by directives.

## 22. Invitation to Bid

The invitation to bid shall, at least, consist of the following:

1. Full name and address of the procuring entity;
2. A brief description of the goods, construction works and services to be obtained,including desired time limit for delivery or completion;
3. Preconditrons to be fulfilled for obtaining the bid documents and the place where such documents are available;
4. The place and deadline for the submission of bid proposals;
5. The place and time for opening of bids, along with an announcement that bidders or representatives are allowed to attend the opening bids,and if the attendants are, however, not present by their own reason,the bids shall not be deterred from opening;
6. The right of the procuring entity shall be reserved to reject the bids partially or fully.

## 23. Bid Documents

1. The bid documents shall contain sufficient information to enable competition among the bids to take place on the basis of complete, neutral and objective terms. In particular, bid documents must include:

ሀ/ የመጫረቻ ሠነድን ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን፣

ለ/ የመጫረቻ ሠነድን ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፣ የጨረታ ሠነዱ የሚላክበትን አድራሻ፣ የጨረታው ሠነድ የሚከፈትበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ፣ እንዲሁም ተጫራቹ ወይም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ ማቅረቢያ ቅፆች፣ እንዲሁም አግባብነት እስካላቸው ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ቅጾች፣

መ/ ከዋናው የመጫረቻ ሠነድ ጋር መቅረብ ያለባቸውን ተጨማሪ ኮፒዎች፣

ሠ/ የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታዎች ፣

ረ/ እንደ አግባብነቱ ዕቃውን ለማቅረብ ወይም ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወስዳል ተብሎ የሚገመተውን ጊዜ ጨምሮ ተፈላጊውን የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር፣

ሰ/ ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት ማለትም የፋይናንስ አቋሙን እና ሕጋዊና ወቅታዊ የንግድ ፈቃድ እንዲሁም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው መሆኑን ለማረጋገጥ ማቅረብ ያለበትን መረጃ፣

ሸ/ ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣

ቀ/ ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን እና ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ፣

በ/ ከጨረታ ውጭ የሚያደርጉ ዋና ዋና ጉዳዮችን (rejection criteria)፣

a) Necessary instructions for the preparation and submission of bids;

b) Information on the final date for receipt of bids, the address to which bids must be sent, the date, hour and place of opening as well as an announcement that bidders or their representatives are allowed to attend the opening ceremony;

c) Forms of bid proposals and, where applicable, forms of bid security to be provided;

d) Additional copies to be submitted with the prgional bid;

e) General and special conditions of the contract;

f) Specification of the required goods and services, including time limit assumed for delivery or completion of the work, as appropriate;

g) Type of evidences, financial stand as well as legal and current trade license to be provided by the bidder to demonstrate its qualification to involve in the bid, and an evidence to ensure that the bidder is given tax payer's identification number;

h) The period during which the bid remains in force;

i) The criteria and the points given to each criterion for evaluation of bids and award of the contract;

j) Main issues those make bidders out of bids;

ተ/ ግዥውን የሚፈጽመው አካል የጨረታውን አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

ቸ/ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ለተፈቀዱ ግዥዎች በውል አፈፃፀም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ እና የዋጋ ማስተካከያው የሚደረግበትን ሁኔታና አፈፃፀሙን፡፡

## 24. የጨረታ ሠነድ ሽያጭ

1) የጨረታ ሠነዶች ለጨረታው ሠነድ ዝግጅት እና ሠነዱን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ ከወጣው ወጪ ባልበለጠ ዋጋ፣ በተፋጠነ ሁኔታ እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርሱ መደረግ አለበት፡፡

2) ግዥ ፈፃሚ አካሉ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ሰነዱ አነስተኛ ከሆነ በነፃ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል።

## 25. በጨረታ ሠነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በራሳቸው ወይም የጨረታታ ሰነድ ከገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላሉ::

2. የተደረገው ማሻሻያ በፅሑፍ ተዘጋጅቶ የጨረታታ ሰነዶችን ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሁሉ በተመሳሳይ ጊዜ መላክ አለበት::

k) A reservation to the effect that the procuring entity may reject the bids partially or completely at any time prior to the notification of award;

l) The price adjustments that may be made during contract implementation and the conditions and the manner under which such price adjustments can be made to special procurement prescribed by the Bureau.

## 24. Provision of Bid Documents

1) Bid documents shall be made available to candidates in an expeditious manner at a price not exceeding the cost of reproduction and delivery to candidates and otherwise in the manner specified in the invitation to bid.

2) Where it deems to be appropriate and small in number the procuring entity may make the bid document available to candidates free of charge.

## 25. Modification to Bid Documents

1. At any time prior to the deadline for submission of bids, the procuring entities may, on their own initiative or in response to an inquiry by a candidate having purchased the bid documents, modify bid documents by issuing an addendum, which becomes an integral part of the bid documents.

2. Any addendum shall be communicated promptly to all candidates having purchased the bid documents at the same time.

3. ግዥ ፈፃሚ አካላት የጨረታታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘውና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን የተረዳ እእንደሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሻሻያውን መሠረት አድርገው የጨረታታ ሰነዱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እእንዲኖራቸው ለማድረግ የጨረታውን ማቅረቢያ ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡

## 26. የጨረታ ማስከበሪያ

1. በዚህ አዋጅ በተለይ ካልተወሰነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት በሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ ተጫራቾች ከመጫረቻ ሠነዶቻቸው ጋር የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው መጠን በጨረታው ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ የማይሳተፉትን ለማስቀረት የሚያስችል ሆኖ፣ ከተወሰነው መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
2. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው ቢኖርም የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ የሚያስፈልግባቸው የግዥ ዘዴዎች እና የጨረታ ማስከበሪያው መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

## 27. የመጫረቻ ሠነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል

1. የመጫረቻ ሠነድ በጽሁፍ ተዘጋጅቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለፀው ቦታ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

3. If the procuring entities consider it necessary to amend the bid documents and if it determines that there is no enough time to incorpotate the modification, they may postpone the closing date by a number of days, depending on the procurement object, which is sufficient to enable the bidders to take the addendum in to account in preparing their bids.

## 26. Bid Security

1. Unless otherwise provided in this proclamation, the procuring entities shall include in the bid documents a condition that bids must be accompanied by a bid security. The amount of such bid security shall be sufficient to discourage irresponsible bidders; it shall be not less than the determined amount.
2. A bid security will be forfeited if a bidder withdraws his bid within the validity period thereof or in the case of a successful bidder, if the bidder repudiates the contract or fails to furnish performance security, if so required.
3. Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, procurement in respect of which bid security is required and the amount of bid security thereof, is to be prescribed by the directive to be issued by the Bureau.

## 27. Submission and Receipt of Bids

1. Bids shall be submitted in writing, signed and in a sealed envelope, to the place and before the deadline stated in the invitation to bid.

2. የመጫረቻ ሰነዱ ሣጥን ውስጥ ሊገባ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ የመጫረቻ ሰነዱን የግዥ ፈፃሚ አካሉ የግዥ ኦፊሰር ተረክቦ ገቢ የተደረገበትን ቀንና ሰዓት የሚያሳይ ማረጋገጫ ለዕጩ ተወዳዳሪው መስጠት አለበት።

3. የመጫረቻ ሰነዱን ለማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሠነድ ሳይከፈት ለተጫራቹ መመለስ አለበት፡፡

## 28. ጨረታን ስለመክፈት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በጨረታ ሠነዱ የተመለከተው ለመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ፣ የመጫረቻ ሠነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የቀረቡ የመጫረቻ ሠነዶችን መክፈት አለበት፡፡

2. ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በመጫረቻ ሰነዱ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ መጋበዝ አለባቸው፡፡

3. የተጫራቹ ስም እና በእያንዳንዱ የመጫረቻ ሠነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ፣ የተሰጠ ቅናሽ እና ግዥ ፈፃሚ አካላት እንደ ግዥው ሁኔታ ተጫራቾች አንፃራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች መረጃዎች ከፍ ባለ ድምጽ መነበብ እና መመዝገብ፣ በጋራ መፈረም እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም የቴክኒክና የፋይንናስ መወዳደሪያ ሀሳብ በሁለት ፓስታታ የቀረበ በሚሆንበት ጊዜ የመጫረቻ ዋጋው የሚከፈተው የቴክኒክ ግምገማው ከተጠናቀቀ በኂላ መሆን አለበት ::

2. The procurement officer of the procuring entity shall give a receipt to the bidder indicating the time and date on which the bid document was submitted, where it becomes impossible to enter the bid document in a bid box.

3. A bid document received after the deadline for submission shall be returned unopened to the bidder.

## 28. Opening of Bids

1. At the time stipulated in the bid documents for opening of bids, which should follow immediately after the deadline for submission of bids, the procuring entity shall open all bids received before the deadline.

2. Bidders or their authorized representatives shall be allowed to attend the opening of bids.

3. The name of the bidder and the total amount of each bid, discounts offered and any such information as the procuring entities deem necessary to let the bidders know their relative rank shall be read out aloud, recorded and signed communal and a copy of the record shall be made available to any bidder on request.

4. Notwithstanding the provisions of sub-article (3) of this Article, the envelope containing the price offered by the bidder shall be opened after the evaluation of the technical proposal where technical and financial proposals are submitted in two separate envelopes.

## 29. የመጫረቻ ሠነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

1. ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ግዥ ፈፃሚ አካላት ተጫራቾች ባቀረቡት የመጫረቻ ሠነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ በመጫረቻ ሠነድ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሃሣብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ግዥ ፈፃሚ አካሉ በጨረታ ምርመራው ወቅት የተገኙ የሂሣብ ስህተቶችን ለማረም ይችላል፡፡ ግዥ ፈፃሚ አካሉ እነዚህን ማስተካከያዎች የመጫረቻ ሠነዱን ላቀረበው ተጫራች በአፋጣኝ መግለጽ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግዥ ፈፃሚ አካሉ ጨረታው የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሠነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው፡፡
4. በጨረታው ሠነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም ግዥ ፈፃሚ አካሉ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአሀዝ ተገልጾ በጨረታ ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

## 29. Examination and Evaluation of Bids

1. The procuring entities may ask bidders for clarification of their bids inorder to assist in the examination and evaluation of bids; however, no change in the substance of the bid, including changes in price, shall be sought, offered or permitted.
2. Nowithstanding sub-article (1) of this Article, the procuring entity shall correct arithmetical errors that are discovered during the examination of bids. The procuring entity shall give prompt notice of any such correction to the bidder that submitted the bid.
3. Without prejudice to sub-article (4) of this Article, the procuring entity may regard a bid as responsive only if it conforms to salient requirements set forth in the bid documents.
4. The procuring entity may regard a bid as responsive even if it contains minor deviations that do not materially alter or depart from the characteristics, terms, conditions and other requirement set forth in bid documents or if it contains errors or oversights that are capable of being corrected without touching on the substance of the bid. Any such deviations shall be quantified, to the extent possible, and appropriately taken account of in the evaluation and comparison of bids.

5. ማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካል ከዚህ በታች የተዘተዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን አሸናፊ አድርጎ መምረጥ የለበትም፡-

ሀ/ ተጫራቹ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተደረገውን የሂሣብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 4 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፡፡

6. ግዥ ፈፃሚ አካሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሠነዱ በተመለከተው ሥርዓት እና የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊው ሁኔታዎችን ያሟሉ የጨረታ ሠነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት፡፡ በጨረታ ሠነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

7. በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው፣

ሀ/ በጨረታ ግምገማ የቴክኒክ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠለት እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች፣

ለ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 7 በፊደል "ሀ" የተመለከተው ቢኖርም በቴክኒክና በዋጋ እንዲሁም በሌሎች መስፈርቶች ተለይቶ ውድድር የሚደረግ ከሆነ ተጫራቾች በእያንዳንዱ መስፈርት ያገኙት ነጥብ ተደምሮ የተገኘው ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተጫራች፣

5. Any procuring entity shall not award a contract when:

a/ the bidder has failed to demonstrate, in the manner provided in sub-article(1) of Article 16 of this Proclamation, that it is qualified;

b/ the bidder does not accept a correction of an arthimetical error made pursuant to sub-article (2) of this article;

c/ without prejudice to sub-article 4 of this Article, the bid is not responsive.

6. The procuring entity shall evaluate and compare the bids that have been held responsive in order to ascertain the successful bid, as defined in sub-article 7 of this Article in accordance with the procedure and criteria set forth in the bid documents. No criterion shall be used that has not been set forth in the bid documents.

7. The successful bid shall be :

a. The bid that is found to be responsive to the technical requirements and with the lowest evaluated price;

b. Notwithstanding sub-article 7(a), if the competition based on technic, value and others among bidders with each criterion, the bidder shall be selected that get the highest result of sum.

ሐ/ ግዥ ፈፃሚ አካሉ በጨረታው ሠነድ ውስጥ አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበትን መስፈርት የገለፀ ከሆነ በጨረታ ሠነዱ የሠፈረውን የጨረታውን ኢኮኖሚያዊ እሴት የሚወስነውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በሚካሄድ ግምገማ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው የጨረታ ሃሳብ ያቀረበው ተጫራች አሸናፊ ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ በፊደል (ለ) የተጠቀሰው መስፈርት በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተና በአሃዝ ሊቀየር የሚችል ሆኖ በግምገማው ሂደት አንፃራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለጽ መሆን አለበት፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በፊደል (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) መሰረት የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስ እና የቴክኒክ አቅም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሲረጋገጥ፣

8. ግዥ ፈፃሚ አካሉ የጨረታ ሠነድ ምርመራና ግምገማውን ውጤት በአጭሩ የሚገልጽ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

## 30. በሚስጥር ስለሚያዙ አሠራሮች

ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ ከማብራሪያ፣ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሣኔ ሃሣብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጢርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፣ አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለጽ የለባቸውም፡፡

c. If the procuring entity has so stipulated in the bid documents, the bid offering better economic advantage ascertained on the basis of factors affecting the economic value of the bid which have been specified in the bid documents, which factors shall, to the extent practicable, be objective and quantifiable the criterion specified sub-article 7 (b) , and shall be given a relative weight in the evaluation procedure or be expressed in monetary terms wherever practicable;

d. Where it is ascertained in post evaluation of bids that the legal, financial and technical standing of the candidate selected as the successful bidder in accordance with sub-article 7(a), (b) or (c) of this Article conforms to the requirements stated in the bid document.

8. The procuring entity shall prepare an evaluation report, containing a summary of the examination and evaluation of bids.

## 30. Process to be confidential

After the opening of bids, information relating to the examination, clarification and evaluation of bids and recommendations for award must not be disclosed to bidders or other persons not officially concerned with this process until the award of the contract is announced.

## 31. ከአሸናፊ ተጫራቾች ጋር ድርድር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከአሸናፊው ተጫራች ጋር የጨረታ ሰነዱ ላይ ባልተጠቀሱ እና መሰረታዊ ይዘቱን በማይለውጡ የውል አፈፃፀም ጉዳዩች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል ።
2. በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 40 ሥር በተጠቀሰው መሰረት በቀጥታ ለሚፈፀም ግዢ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ግዥ ፈፃሚ አካሉ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ አይችልም።

## 32. ተጫራቾችን አሸናፊ ለማድረግ ያቀረቡትን የመወዳደሪያ ሃሣብ አሻሽለው እንዲያቀርቡ መጠየቅ የማይቻል ስለመሆኑ

ማናቸውም ተጫራች በጨረታው ሠነድ ከተመለከተው ውጭ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለውጥ ወይም በሌላ አኳኋን ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንኑ ለመፈፀም ግዴታ እንዲገባ በቅድመ-ሁኔታነት ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም፡፡

## 33. አሸናፊነትን ስለመግለጽና ውል ስለመፈራረም

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የመወዳደሪያ ሃሣቡ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን መግለጽ አለባቸው፡፡ ለተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታው አሸናፊ ተጫራች የአሸናፊነት ምክንያት የሚገልጽ ማስታወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

## 31. Matters Subject for Negotiation with the Successful Bidder

1. The procuring entities may negotiate with the successful bidder on matters of contract that not mentioned and change the fundamental content of the bid document.
2. Except in a single source procurement provided for in Article 40 of this proclamation the procuring entity may not negotiate on the price offered by the successful bidder and on other issues related to price.

## 32. No Possible to Request Bidders Modify Their Presented Proposals by Assuming to Make them Winners

Any bidder, to be winner, shall not be requested or obliged to change the value of bid or modify the presented proposal by other means or to implement by obligation as a precondition, unless otherwise stated at the bid document.

## 33. Notification of Award and Signing of Contract

1. Prior to the expiry of the period of bid validity, the procuring entity shall notify the successful bidder that its bid has been accepted. The unsuccessful bidders shall be informed who the successful bidder is and why he has won the bid.

2. በግዥ ፈፃሚ አካሉ እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመሥርቷል የሚባለው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የውል ሠነድ ሲፈረም ይሆናል፡፡

3. ግዥ ፈፃሚ አካሉ ለተሸናፊዎቹ ተጫራቾች ተሸናፊነታቸውን የሚገልፀው ማስታወቂያ ከመድረሱ እና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የግዥውን ውል መፈረም የለበትም፡፡

4. ግዥ ፈፃሚ አካሉ የውል አስተዳደርን በሚመለከት ሊከተል የሚገባውን አሠራር ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

## 34. የውል ማስከበሪያ

አቅራቢው በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ምክንያት በግዥ ፈፃሚ አካሉ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል የውል ማስከበሪያ ለግዥ ፈፃሚ አካሉ መስጠት አለበት፡፡ የውል ማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ ዓይነቶች፣ የውል ማስከበሪያ ዓይነትና መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 35. የቅድሚያ ክፍያ

1. በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም ለአቅራቢው የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠን እና አፈፃፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. የቅድሚያ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው ቢሮው በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር አቅራቢው በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚወሰደው ገንዘብ መጠን ጋር እኩል የሆነ ዋስትና ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

2. The existence of a contract shall be confirmed through the signature of a contract document incorporating all agreements between the parties.

3. The contract shall not be signed by the procuring entity prior to the receipt of the notice by the unsuccessful bidder and before the period specified in the directive to be issued by the bureau has lapsed.

4. The procedures that procuring entity has to follow in administering the contract shall be prescribed by a directive to be issued by the Bureau.

## 34. Contract Security

A supplier shall provide the procuring entity with a contract security to make good on any default by the supplier under the contract. The type of procurement for which contract security is required and the type and amount of contract security shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

## 35. Advance Payment

1. The amount of advance payment that may be allowed to suppliers in public procurement and the manner in which it is made available shall be determined by the directive to be issued by the Bureau.

2. Unless, otherwise the Bureau allows with a special condition, advance payment may be effected only where a supplier furnishes advance payment guarantee in an amount equal to the advance payment.

## ምዕራፍ አራት

## ውስን ጨረታ

### 36. በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ከዚህ በታች ከተመለከቱት ሁኔታዎች መካከል ቢያንስ አንዱን ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን ወይም፣

ለ/ በርካታ የጨረታ ሠነዶችን ለመመርመር እና ለመገምገም የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ጊዜ ዕቃው፣ የግንባታ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከሚያወጣው አነስተኛ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን ሆኖ ሲገኝ፣ይህ ሊፈጸም የሚችለው የግዥው ዋጋ ግምት በግዥ መመሪያው ከተመለከተው ጣሪያ ያልበለጠ ሆኖ ሲገኝ ነው።

ሐ/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ የሚገለፅ ሆኖ በተደጋጋሚ ግልጽ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ያልተገኘ ሲሆን፡፡

### 37. የውስን ጨረታ አፈፃፀም

የውስን ጨረታ ሥርዓቶች ከግልጽ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ ውስን ጨረታ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ልዩ አሠራሮች የሚከተል ይሆናል፡-

1. የጨረታ ጥሪው በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጎት ላላቸው ለተወሰኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቻ ይላካል፡፡ ተጫራቾች አድልዎ በሌለበት ሁኔታ በአቅራቢዎች ዝርዝር ከተመዘገቡት አቅራቢዎች መካከል መመረጥ ይኖርባቸዋል፡፡

## CHAPTER FOUR

## RESTRICTED TENDERING

### 36. Conditions For Use of Restricted Tendering

Procuring entities may use restricted tendering as a method of procurement at least one is satisfied from the following conditions:

a) It is ascertained that the required object of procurement is available only with limited suppliers,

b) Restricted tendering shall be applied, when the cost and time for examination and evaluation of many bid documents is higher than the value of the required object of procurement. It shall be applicable when the assuming value of procurement not exceed with the specified value on the procurement directive;

c) Where a repeated acvertisement of the invitation to bid fails to attract bidders in respect of procurement subject to the directive to be issued by the Bureau.

### 37. Procedure For Restricted Tendering

Restricted tendering procedures are the same as those applied in open tendering, except that:

1. The invitation to bid is addressed to a limited number of qualified candidates which have declared an interest in submitting bids. The selection should be made in a non discriminatory manner among those registered in the suppliers list.

2. ግዥ ፈፃሚ አካላት በውስን ጨረታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ የሚደረግላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመርጡት ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውንና የሚፈለገውን ግብር የከፈሉ ሆነው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቸው፣ ከአገልግሎት አሰጣጥና ከዕቃ አቅርቦት ተሞክሯቸው መልካም ዝና ካላቸው እና ከአቅራቢዎች ዝርዝር ከተመዘገቡ መካከል ይሆናል፡፡ አመራረጡ ለነዚህ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊ የሆነ እድል የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ግዥ ፈፃሚ አካሉ የግዥውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የጨረታ ማስከበሪያ ማቅረብ የሚያስፈልግ መሆን ያለመሆኑን ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ

### 38. በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ግዥው በመመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ ዕቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ሲሆኑ ነው፡፡

### 39. በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ አፈፃፀም

1) ግዥ ፈፃሚ አካላት በአቅራቢዎች ዝርዝር ከተመዘገቡ አቅራቢዎች መካከል ቢያንስ ሦስት አቅራቢዎችን የዋጋ ማቅረቢያ እንዲሰጡ ሊጠይቁ ይገባል፡፡

2) The procuring entities shall select candidates from among those who have legal trade license, have paid the required tax and have tax payer's identification number, have good reputation from their service delivery, and goods supply and among those registered in the suppliers list. The selection shall be obtaining justifiable chance for the candidates.

3) The procuring entity may decide, depending on the circumstances, if bid security will have to be submitted or not.

## CHAPTER FIVE
## REQUEST FOR QUOTATION

### 38. Conditions For Use of Request For Quotations

Procuring entities may engage in procurement by means of request for quotations for the purchase of readily available goods or for procurement of works or services for which there is an established market, so long as the estimated value of the contract does not exceed an amount stated in the procurement directive.

### 39. Procedure for Request of Quotations

1. Procuring entities shall request quotations at least three from among suppliers registered in the suppliers list.

2. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም አንድ አይነት ግዥ አማራጭ አቅራቢዎች እስካሉ ድረስ በተደጋጋሚ የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በመጋበዝ ማወዳደር አይቻልም:: በመሆኑም ግዥ ፈፃሚ አካሉ እስከተቻለ ድረስ በዘርፉ ለተሰማሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ የመወዳደር ዕድል መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚላከው መጠየቂያ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜ እና የውል ቃሎች እንዲሁም ሌሎች የግዥ ፈፃሚ አካላትን ፍላጐቶች ዝርዝር የሚገልፅ መሆን አለበት::
4. ግዥ ፈፃሚ አካሉ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል::
5. ግዥ ፈፃሚ አካሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች አሟልቶና አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተወዳዳሪ የግዥ ትዕዛዝ ይሰጣል::

## ምዕራፍ ስድስት

## በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ

### 40. በቀጥታ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. የግዥ ፈፃሚ አካላት በቀጥታ ግዥ የሚፈጽሙት በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ግዥ ፈፃሚ አካላት በቀጥታ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡-

2. In cases where procurements are made using request for quotation, as long as other suppliers, who can supply the same goods, services or works are available, the procuring entity shall not repeatedly invite the same suppliers to submit their quotations. The procuring entity shall ensure that equal opportunity of participation in public procurement is given to all candidates engaged in the business.

3. The request shall contain a clear statement of the requirements of the procuring entities as to quality, quantity, terms and time of delivery of the goods and other services,

4. The procuring entity shall give adequate time to candidates in which to prepare their quotations.

5. A purchase order shall be placed with the candidate who meets the requirements of the procuring entity stipulated in sub-article 3 of this Article.

## CHAPTER SIX

## DIRECT PROCUREMENT

### 40. Conditions For Use of Direct Procurement

1. The procuring entities shall not use direct procurement in accordance with there is no competition among candidates or by assuming to make difference among them. However, procuring entities use direct procurement for the following conditions:

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ የተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣው መመሪያ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለዕቃዎች አገልግሎቶች ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ ዕቃዎችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈለግና ይህም ከሌላ አቅራቢ ግዥው ቢፈፀም የሚገዛው መሣሪያ ወይም አገልግሎት ግዥ ፈፃሚ አካሉ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም ከአገልግሎቱ ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያ አቅራቢ ተጨማሪ አቅርቦቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

ሐ/ በግዥ መመሪያው የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ አስቀድመው ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እና በቴክኒካዊ ወይም በኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሠራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

መ/ አሸናፊው በግልጽ ወይም በውስን ጨረታ ዘዴ ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራዎች ወይም አቅርቦቶች በድጋሚ እንዲሠሩ ወይም እንዲቀርቡ ማድረግ በማስፈለጉ ተጨማሪ ውል መፈፀም አስፈላጊ ሲሆን፣

a) Where in the absence of competitions for technical reasons the goods, works or Services can be supplied or provided only by one candidate;

b) Without prejudice to the directive limits to be issued pursuant to this proclamation, for additional deliveries of goods by the original supplier which are intended either as parts of replacement for existing supplies, services or installations or as the extension of existing supplies, services or installation where a change of supplies would compel the procuring entity to procure equipment or services not meeting requirements of interchangeability with already existing equipment or services;

c) Within limits defined in the procurement directive, when additional works, which have been not included in the initial contract have, through unforeseeable circumstances, become necessary since the separation of the additional works from the initial contract would be difficult for technical or economic reasons;

d) After the selection of successful bidder with open or restricted bidding, for new works consisting of the repetition of similar works which conform to a basic project of which an initial contract has been awarded;

| | |
|---|---|
| ሠ/ የመጀመሪያው የምክር አገልግሎት ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ በመጠናቀቁ ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ አገልግሎቱን መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ | e) For continuation of consultant services, where the original contract has been satisfactorily performed and the continuation is likely to lead to gains in economy and efficiency; |
| ረ/ ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ጥቃቅን ግዥዎች ሲያጋጥሙ፣ | f) Compell the conditions and if the procurements not incorporated in procurement plan; |
| ሰ/ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና ለግዥ ፈፃሚ አካሉ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም የዕቃ ግዥ ሲሆን፣ | g) For purchase of goods made under exceptionally advantageous conditions for procuring entity which only arise in the very short time; |
| ሸ/ በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በግዥ ፈፃሚ አካላት የሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በግዥ ፈፃሚ አካላት የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፣ | h) The head of the procuring entities has determined that the need of pressing emergency in which delay would create serious problems and therefore injurious to the performance of that procuring entities; |
| ቀ/ ግዥ ፈፃሚ አካላት ለሚኖራቸው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ በባህላዊ ወይም በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፡፡ | i) Where situations arise in which shopping becomes necessary to meet the special procurement needs of procuring entities. |
| 2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በፊደል “ቀ” የተመለከተው በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሠማሩ ድርጅቶች ለሚሸጧቸው ዕቃዎች ግዥ የሚያገለግል ሲሆን በመደበኛ አቅራቢነት ከተሠማሩ አቅራቢዎች አዘውትረው የሚፈፀሙ ግዥዎችን አይጨምርም፡፡ | 2. The specified provision sub-article 1(i) of this Article used to cover unusual disposals by firms, which are not normally suppliers and it is not intended to cover routine purchases from regular suppliers. |
| 3. በመመሪያ የሚገለፀዉ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1(ቀ) መሠረት በቀጥታ ለሚፈፀሙ ግዥዎች ዉል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡ | 3. With in limits defined in the procurement directives, it shall not be necessary to conclude a contract in respect of direct procurements in accordance with sub- Article 1(i) of this Article. |
| 4. ግዥ ፈፃሚ አካላት ይህ የግዥ ዘዴ በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ | 4. Procuring entities shall ensure that this method is not resorted to with a view to avoiding possible competition or in a manner which would constitute a means of discrimination among candidates. |

## 41. በቀጥታ የሚከናወን ግዥ አፈጻጸም

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት በቀጥታ ግዥ ለመፈፀም ሲፈልጉ ግዥውን መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር በግልፅ መደራደር አለባቸው::
2. በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ ግዥ ለመፈፀም የሚደረሰው ስምምነት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ውል መረጋገጥ አለበት::
3. በቀጥታ ለሚፈፀም ግዢ ድርድር የማድረጊያ አትኩሮተ-ነጥቦች ዝርዝር በየደረጃው ባሉ ግዥ ፈፃሚ አካላት የበላይ ኃላፊዎች ፀድቆ ለተደራዳሪዎች ሊሰጥ ይገባል።

## ምዕራፍ ሰባት

## በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

### 42. በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ከአንድ ግዢ ውል ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ድርሻ 50% /ሃምሳ በመቶ/ እና ከዚያ በላይ ሲሆን ነው::

## 41. procedure for Direct procurement

1. When procuring entities engage in direct procurement according to Article 40 (1) of this proclamation, it shall prepare a description of its needs and any special requirements as to quality, quantity, terms and time of delivery, and shall be free to negotiate on price and conditions of offer with the sole candidate.
2. Without prejudice to the provisions of sub-article 4 of article 40 of this proclamation, any agreement reached to conduct the procurement shall be confirmed by a contract signed by both parties.
3. The salient points to focus on in the negotiation of contracts for direct procurements shall be approved by the head of procuring entities in different levels concerned and communicated to the negotiators.

## CHAPTER SEVEN

## REQUEST FOR PROPOSALS

### 42. Conditions for Use of Request for Proposal

Procuring entities may engage in procurement by means of request for proposals from one general amount contracts for which the component of consultancy services represents 50% and more amount of the contract.

## 43. በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ የሚከናወን ግዥ አፈፃፀም

1. የመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ ከሦስት ላላነሱ እና ከሰባት ላልበለጡ አቅራቢዎች በግዥ ፈፃሚ አካሉ ለሚመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ይኖርበታል፡፡ የምክር አገልግሎቱ የሚጠይቀዉ ወጪ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተወሰነዉ የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ እጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በዉድድሩ ተሣታፊ ለመሆን የሚፈልጉት ሁሉ ሃሣባቸዉን እንዲገልፁ ከተጠየቀ በኋላ ይሆናል፡፡
2. የመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣
   ሀ/ የግዥ ፈፃሚውን አካል ሙሉ ስምና አድራሻ፣
   ለ/ የሚፈለገውን አገልግሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ጽሁፍ፣
   ሐ/ የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ በዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከምክር አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸውን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፣
   መ/ የመወዳደሪያ ሃሣቦችን፣ መገምገሚያ ስፈርቶችን፣ ለዋጋና ለሌሎች መሥፈርቶች የሚሰጠውን ነጥብ፣ መስፈርቶቹ መወዳዳሪያ ሃሣብ በሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን አኳኋን፣
   ሠ/ የመወዳደሪያ ሃሣብ የሚቀርብበትን ቦታና የመጨረሻ ቀን፣

## 43. Procedure for Request for proposals

1. Request for proposals shall be addressed to not less than three and not more than seven candidates selected by the procuring entity. The selection of candidates for consultancy services above a threshold to be determined by a directive to be issued shall be made after inviting candidate with notice to submit expression of interest.
2. A request for proposals shall contain at least the following information:
   a) The full name and address of the procuring entity;
   b) Description of the services required, normally through terms of reference;
   c) In the case of consultancy assignments which may involve potential conflicts of interest, a reminder that candidates for such assignments must exclude themselves from procurement of goods and works which may follow as a result of or in connection with the consultancy agreement;
   d) The criteria for evaluating the proposals, the relative weight to be given to price and other criteria, and the manner in which they will be applied in the evaluation of proposals;
   e) Place and deadline for submmission of proposals.

3. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሃሣብ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
4. ግዥ ፈፃሚ አካሉ አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሃሣቡ ውስጥ የተመለከተውን የአገልግሎት ባህሪ፣ መጠን እና አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማካሄድ ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ መፍቀድ ይችላል፡፡
5. ግዥ ፈፃሚ አካሉ በአሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ ሠነድ በተመለከተው የመገምገሚያ መስፈርት እና ሥርዓት መሠረት በሚካሄደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሣብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን ተወዳዳሪ ነው፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ

### 44. በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 በተመለከተው መሠረት በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥን ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

1. ለሚገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በግዥ ፈፃሚ አካላት ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና ግዥ ፈፃሚ አካላት የግዥ ፍላጐትን በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሔ ለማግኘት፤

3. Candidates shall be given adequate time in which to prepare their proposals.
4. The procuring entity may negotiate or allow to be revised with the first ranked candidate with respect to the nature, volume and organization of the services included in their proposals.
5. Any award by the procuring entity shall be made to the candidate whose proposal is most advantageous, determined in accordance with the criteria and procedures for evaluating proposals set forth in the request for proposals.

## CHAPTER EIGHT
## TWO-STAGE BIDDING

### 44. Conditions for Use of Two-Stage Bidding

Procuring entities, pursuant to Article 45 of this proclamation, may engage in procurement by means of two-stage bidding:

1. When it is not feasible for the procuring entities to formulate detailed specifications for the goods or works and in the case of services, to identify their characteristics and, in order to obtain the most satisfactory solution to its procurement needs;

ሀ/ ጨረታን፣ የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦት መወዳደሪያ ሃሣብን በሥራ ላይ ማዋል ሲፈለግ፣

ለ/ በሚገዙት ዕቃዎች፣የግንባታ ሥራዎች፣ የምክርና እና ሌሎች አገልግሎቶች ባህርይ ወይም ተፈጥሮ አስመልክቶ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ፡፡

2. ግዥው የሚካሄደው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለማምረት ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት እስካልሆነ ድረስ ግዥ ፈፃሚ አካሉ የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ፡፡

3. ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ ተጫራቾች ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና ይህም የሆነው ግዥ ፈፃሚ አካሉ የተሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፡፡

## 45. <u>የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ አፈፃፀም</u>

1. ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን፣ በጨረታው ሠነድ ተጫራቾች በመጀመሪያው ደረጃ ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲያቀርቡ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በጨረታው ሠነድ አቅራቢዎች ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መግለጫዎች፣ ጥራት ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህርያት እንዲሁም የአቅርቦቱን ውል ቃሎችና ሁኔታዎች እና አግባብነት እስካለው ድረስ የአቅራቢውን የሙያ እና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልፁ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

a) When it needs to implement the bids, goods and services supplies proposals;

b) When it needs to negotiate with candidates in accordance with the nature or conduct of the procuring goods, works, consultation and other services.

2. When the procuring entity seeks to enter into a contract for the purpose of research, experiment, study or development, except where the contract includes the production of goods in quantities sufficient to establish their commercial viability or to recover research and development costs;

3. Where bid proceedings are initiated but no bids are submitted or where all bids are rejected due to failure on the part of the procuring entity concerned to draw up a clear and complete specification;

## 45. <u>Procedure for Two-Stage Bidding</u>

1. The solicitations documents shall call upon suppliers to submit, in the first stage of the Two-stage bidding proceedings, initial tenders containing their proposals without a tender price. The solicitation documents may solicit proposals relating to the technical, quality or other characteristics of the goods, works or services as well as to contractual terms and conditions of supply and where relevant the professional and technical competence and qualifications of the suppliers.

2. በሁለት ደረጃ ጨረታ ዘዴ በሁለተኛዉ ደረጃ ላይ ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካሉ የጨረታ ሀሳባቸው ውድቅ ያልተደረገባቸውን ተጫራቾች አንድ የተለየ ዝርዝርን በሚመለከት ዋጋ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል፡፡ ይህንን የተለየ ዝርዝር ሲያዘጋጅ ግዥ ፈፃሚ አካሉ በመጀመሪያው የጨረታ ሠነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህርያት እና ሠነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት መሥፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሠረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማሙ አዳዲስ ባህርያትንና መስፈርቶችን ለመጨመር ይችላል፡፡

3. እንደዚህ ያሉት ማናቸውም ስረዛዎች፣ ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መገለጽ አለባቸው፡፡ የመጨረሻ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ ለማቅረብ ያልፈለገ ማናቸውም አቅራቢ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ሳይደረግበት ከጨረታው ውድድር እራሱን ሊያገል ይችላል፡፡

4. በሁለት ደረጃ ጨረታ አሸናፊውን ተጫራች ለመወሰን ግምገማ እና ውድድር የሚደረገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

5. ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል፡፡



2. In the second stage of the two-stage tendering proceedings, procuring entities shall invite supplier whose bids have not been rejected to submit final tenders with parties with respect to a single set of specifications. In formulating those specifications, procuring entities may delete or modify any aspect originally set forth in the solicitation documents of the technical or quality characteristics of the goods, works, or services to be procured and any criterion originally set forth in those documents for evaluating and comparing bids and for ascertaining the successful bids and may add new characteristics or criteria that conform with this proclamation.

3. Any such deletion, modification or addition shall be communicated to suppliers in the invitation to submit final bids. A supplier not wishing to submit a final bid may withdraw from the bid proceedings without forfeiting any bid security that the supplier may have been required to provide.

4. The final bids shall be evaluated and compared in order to ascertain the successful bidder pursuant to Article 29 of this proclamation.

5. The procuring entity may engage in negotiation with the first ranking bidder concerning any aspect of its bid, except price.

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## በዓለም ዓቀፍ ውድድር የሚፈፀም ግዥ

### 46. ዓለም ዓቀፍ ግዥ

1. ዓለም ዓቀፍ ግልጽ የጨረታ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የውጭ ኩባንያዎች በጨረታው ተሣታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በግልጽ ጨረታው ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል የታመነበት እና ግዥው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተዉ የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነዉ፡፡
2. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 3 ሥር የተጠቀሱትን እንዲሁም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሥርዓቶች መከተል አለበት፡-

ሀ/ የጨረታ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነዶች የዓለም ዓቀፍ ንግድ መገልገያ በሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚታተም፣ በቂ ሥርጭት ባለው እና ዓለም ዓቀፍ ውድድርን በሚጋብዝ ጋዜጣ እንዲሁም በመመሪያው ላይ በሚገለፀው መሠረት በቢሮው ድህረ-ገጽ እንዲወጣ መደረግ አለበት፡፡

ሐ/ የመጫረቻ ሠነድ የማቅረቢያ ጊዜው የጨረታው ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣባቸውን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚያስፈልጋቸውን በቂ ጊዜ የሚፈቅድ መሆን አለበት፡፡

## CHAPTER NINE

## INTERNATIONAL COMPETITIVE BIDDING

### 46. Open International Bidding

1. Open international bidding shall be used whenever in open bidding an effective competition cannot be obtained unless foreign firms are invited to bid and for procurements above a threshold to be determined by a directive to be issued by the Bureau.
2. Open international bidding shall observe the provisions of chapter 3 as well as the following procedures:

a) The invitation to bid and the bid documents shall be prepared in the English Language;

b) The invitation to bid shall be advertised in a news paper published in English Language which has world wide circulation and attracts foreign competition as well as on the Bureau's website in the manner prescribed in the directive;

c) The time allowed for submission of bids shall be sufficient for the invitation to reach candidates and for enabling them to prepare and submit bids;

መ/ የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር ከአገር ውስጥ ደረጃዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ እስከተቻለ ድረስ በዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ወይም በዓለም ዓቀፍ ንግድ በስፋት የሚሠራበትን ደረጃ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ሠ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸውን እንዲሁም የሚያቀርቡበትን ማናቸውንም የዋስትና ሠነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በጨረታ ሠነዱ በተመለከተው እና በዓለም ዓቀፍ ንግድ በስፋት በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት፡፡

ረ/ አጠቃላይ እና ልዩ ልዩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በዓለም ዓቀፍ ንግድ የሚሠራባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በሚያዘዉ መሠረት ግዥዉ መመሪያዉ ከወሠነዉ የገንዘብ መጠን በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይንም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑ ከተረጋገጠ ግዥው በአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ሊካሄድ ይችላል።

4. ለየግዥ ዘዴው የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ እና የውጪ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል ሲታመንበት ግዥ ፈፃሚ አካላት በውስን ጨረታ፣ በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ ወይም በቀጥታ በሚፈፀም ግዥ ዘዴ በመጠቀም ግዢውን በዓለም ዓቀፍ ውድድር መፈፀም ይችላሉ፡፡

d) Technical specifications of the goods, works and services shall be compatible with national requirements, and conform as far as possible with international standards or standards widely used in international trade;

e) Candidates shall be permitted to express their bids, as well as any security documents to be presented by them in Ethiopian Birr, or in a currency widely used in international trade and stated in the bid documents;

f) General and special conditions of contract shall be of a kind generally used in international trade.

3. Pursuant to sub-article (1) of this Article, procurement may be effected by means of national competitive bidding not withstanding that the cost of the procurement exceeds the threshold established in the directive for national bidding if it is ascertained that the required object of procurement is available only locally.

4. Conditions for using other methods of procurement than open bidding are satisfied, procuring entities may conduct procurement through international competitive bidding by means of restricted tendering, request for proposals, or direct procurement where it is ascertained that it is impossible to carry out effective procurement without the participation of foreign companies.

## ምዕራፍ አስር

## ልዩ ግዥ

### 47. ልዩ ከፍተኛ ግዥዎች

1. ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ልዩ ከፍተኛ ግዥዎች፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚፈለጉ ተመሳሳይ አቅርቦቶችን እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶችን ሽያጭ የሚፈጽም አካል የክልል መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይቋቋማል::

2. ቢሮው ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በሚቋቋመው አካል የሚፈፀሙ ግዥዎችን ዓይነት ይወስናል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### 48. የማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም

1/ ከአንድ በላይ በሆኑ ግዥ ፈፃሚ አካላት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሚከናወኑ ተመሳሳይ አቅርቦቶች የማዕቀፍ ስምምነት በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል፡-

ሀ/ ቢሮው ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚኖራቸውን ተመሳሳይ ፍላጎት በማጥናት የዕቃና አገልግሎቶች ዝርዝር ያወጣል፤ በየጊዜውም ዝርዝሩን ያዳብራል።

ለ/ ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱት ዕቃና አገልግሎቶች የሚኖራቸውን የፍላጎት ትንበያ አዘጋጅተው ግዥውን እንዲያከናውን ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያሳውቃሉ።

## CHAPTER TEN

## SPECIAL PROCUREMENT

### 47. Large Value Procurement

1. There shall be established a central body, which shall be in charge of the execution of large value procurements having regional significance procurements of supplies for which a demand is shown by more than one procuring entity and sale of public property to be disposed off, by the council of Regional Government.

2. The Bureau shall identify and update the types of procurements to be executed on account of their regional significance by the central body which shall be established pursuant to sub-article (1) this Article.

### 48. Procedure of Framework Contract

1. The following procedure of framework contract shall be followed to meet similar procurement requirements of more than one procuring entities within a given time frame:

   a) The Bureau shall undertake a survey of the similar requirements of procuring entities, issue a list of goods and services constituting such requirements and update the list regularly;

   b) Procuring entities shall prepare a forecast of their requirements of goods and services falling under the list mentioned in subarticle1(a) of this Article and communicate the same to the body authorized to conduct large procurements;

ሐ/ በአንቀፅ 47 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋመዉ አካል የማዕቀፍ ስምምነት ይፈፅማል፤ያስተዳድራል፡፡

መ/ ግዥ ፈፃሚ አካላት የተፈረመውን የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈለገ ጊዜ የግዥ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ግዥያቸውን ይፈፅማሉ።

ሠ/ ግዥ ፈፃሚ አካላት ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው የግዢ ትዕዛዝ የሚያስተላልፉት የማዕቀፍ ስምምነቱ ከተፈፀመበት ዋጋ፣ የክፍያ እና ሌሎች የአፈፃፀም ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይሆናል።

2/ በግዥ ትዕዛዝ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 19 በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ከማዕቀፉ ስምምነት የነጠላ ዋጋ ወይም መሰረታዊ በሆኑ ሌሎች የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማድረግ አይፈቀድም። ሆኖም በማዕቀፍ ስምምነቱ ያልተካተቱ እና በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የማያስከትሉ ጉዳዮች ግዥ ፈፃሚ አካሉ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በሚያደርጉት ስምምነት ይወሰናሉ::

3/ የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀመው በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ሆኖ፣ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ፀንቶ ሊቆይ ይችላል::

c) The body to be established in accordance with Article 47(1) of this proclamation shall conclude and administer framework contracts;

d) Procuring entities shall on the basis of the framework contract signed by the central body of procurement conclude the procurement by making order with the suppliers of goods and services that they require;

e) The order that procuring entities place with the suppliers for goods and services of their requirements under the framework contract shall confirm to the terms of the framework contract regarding price, terms of payment and other matters related to the execution of procurement.

2. Except in cases provided in Article 19 of this Proclamation, procuring entities shall not be allowed to vary unit prices and such other fundamental terms of the framework contract when placing order for goods and services. However, the procuring entity and the supplier may agree on terms that have not been dealt with in the framework contract or that do not materially affect the framework contract.

3. The framework contract shall be awarded through open bidding procedure and may remain valid for three years.

4/ አንድ ግዥ ፈፃሚ አካል በተደጋጋሚ ለሚኖረው የግዥ ፍላጐት ግዥን በማዕቀፍ ስምምነት ሊፈፅም የሚችለው በቢሮዉ በሚወጣ መመሪያ የተመለከተውን የዕቃ ወይም የአገልግሎት ዋጋ የሚወስንበትን ግልፅ መስፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## የመንግስት ንብረት አስተዳደር

### 49. ጠቅላላ

የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ የመንግስትን ንብረት በአግባቡ የመያዝ እና የመጠቀም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የማስወገድ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

### 50. ንብረትን ስለመያዝ

1. ማናቸውም የመንግስት ንብረት በባለቤትነት የመያዝ ብቸኛ ዓላማ በግዥ ፈፃሚ አካሉ የፀደቁትን ፕሮግራሞች ለማስፈፀም እና አገልግሎቱን በማፋጠን ውጤታማና ብቁ ለማድረግ መሆን አለበት፡፡
2. ቢሮው በማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካል ሥር ያልሆኑትን የክልል መንግሥት ንብረቶች በመንግስት ንብረትነት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝም እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

### 51. የንብረት አጠቃቀምና ጥገና

1. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ ማናቸውም የመንግስት ንብረት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለበት።
2. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

4. In procuring goods and services under a framework contract to fulfill their recurrent requirements, procuring entities shall have to adhere to the criterion of fixing prices of goods and services to be determined in the directive to be issued by the Bureau.

## CHAPTER ELEVEN
## PUBLIC PROPERTY ADMINISTRATION

### 49. General

The head of procuring entity shall ensure that property at the disposal of the public body is properly handled, used and where necessary, disposed off.

### 50. Acquisition

1. All acquisitions of public property shall be for the sole purpose of facilitating the delivery and maintenance of approved programs by procuring entity as efficiently and effectively as possible.
2. The Bureau shall account for, administer and where necessary, dispose off property of the Regional Government which are not administered by any other procuring entity.

### 51. Use and Maintenance of Property

1. The heads in different levels shall ensure that all public property is used as productively as possible.
2. The heads in different levels shall establish a proper maintenance system for all public property to ensure that it will operate as economically and effectively as possible.

## 52. የመንግስት ንብረት የማስተዳደር ኃላፊነት

1. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ለማስተዳደር የሕይወት ዘመን ሥርዓትን ይከተላል።
2. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ከተያዘበት፣ ከአገልግሎት ውጪ እስከሆነበት ቀን ድረስ ንብረቱ አገልግሎት ያቋረጠበትን ጊዜ፣ የንብረቱን አይነት ፣ ብዛቱን እና ያስከተለውን ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን ማረጋገጥ አለበት።
3. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ ማናቸውንም ንብረት እንዲገለገሉበት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች መሰጠቱን እና በቋሚ ንብረት መዝገብ መስፈሩን ማረጋገጥ አለበት።
4. ማናቸውም የመንግስት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መቆጠር አለበት።
5. የመንግስትን ንብረት ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሳይቻል ሲቀር ግምቱ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።
6. ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ በመንግስት ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ ይሰላል::
7. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ያለ አግባብ እንዳይከማች ማረጋገጥ አለበት።

## 53. ንብረትን መጠበቅና መንከባከብ

ማናቸውም የበላይ ኃላፊ እና ሠራተኞች የመንግስትን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው።

## 52. Responsibility of Public Property Management

1. The heads in different levels shall adopt a life –time approach to the management of public property.
2. The heads in different levels shall ensure that items of public property are recorded as to date, description, quantity and cost from acquisitions to the end of their life-time.
3. The heads in different levels ensure that the custodial responsibility for each fixed asset acquired is assigned to persons using such fixed assets and are recorded in the register of fixed assets.
4. All inventories of public property shall be physically verified against records at least annually.
5. Where the actual cost of public property is not determinable, its cost shall be estimated in accordance with the directive to be issued by the Bureau.
6. The depreciation value shall be calculated on the public fixed asset in accordance with the execution of particular derective to be issued by the Bureau.
7. The heads in different levels ensure that the public property shall not be deposited un properly.

## 53. Protection and Preservation of Property

The heads and all employees are responsible for the protection and preservation of public property.

## 54. ንብረትን ማስወገድ

1. በየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መወገዳቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የተወገደ የመንግስት ንብረት መግለጫና ንብረቱን በማስወገድ የተገኘው ገንዘብ በመንግስት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለል አለበት።
3. የመንግስትን ንብረት በማስወገድ የተገኘ ገቢ ወደ ክልሉ መንግስት ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ አለበት፡፡ሆኖም በከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች በሽያጭ ከሚወገዱ ንብረቶች የሚገኘው ገቢ የከተማ አስተዳደሮቹ ወይም ማዘጋጃ ቤቶቹ ሃብት ይሆናል።
4. የግዥ ፈፃሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት የማስወገዱ ተግባር ከአቅም በላይ መሆኑን ካረጋገጠ በሦስተኛ ወገኖች አማካኝነት ሊፈፅም ይችላል::

## 55. ንብረትን መሰረዝ

1. የመንግስት ንብረት ለሚገኝበት መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ መስሪያ ቤት የማይጠቅምና ዋጋ የማያወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሰረዛል።
2. የመንግስት ንብረት ከጥቅም ውጭ መሆኑ ወይም መጥፋቱ ሲረጋገጥ ከንብረት መዝገብ ይሠረዛል።ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
3. ማናቸውም የመንግስት ንብረት ሲሰረዝ መግለጫውና የንብረቱ የመዝገብ ዋጋ በመንግስት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃልሎ መታየት አለበት።

## 54. Disposal of Property

1. The heads in different levels ensure that fixed assets which are not useful to the organization are disposed off.
2. The description and amount received from all public property disposed off shall be included in the public accounts.
3. Concerning the matter, proceeds from the disposal of public property shall be deposited in to the account of the regional state treasury; whereas, the revenue from sales of disposal of properties of the city administrations and municipalities shall be the property of the city administrations and municipalities.
4. The head of procuring entity shall use third parties if it ensured the disposal of property is out of the scope.

## 55. deletion Property

1. Where public property is considered to be of no use in the public body or elsewhere, and has no-scrap value, it shall be deleted in accordance with the directive to be issued by the Bureau.
2. Deletion of public property shall be recorded when destruction or losses take place. Detailed implementation shall be issued by directive.
3. The description and book value of all public property deleted shall be included in the public accounts.

# ምዕራፍ አስራ ሁለት
# በመንግስት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት ስለሚቀርብ አቤቱታ

## 56. ጠቅላላ

1. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግዥውን በፈፀመው ወይም ንብረቱን በሚያስወግደው አካል የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር ይህን አዋጅ፣ ቢሮው የሚያወጣውን የማስፈፀሚያ መመሪያ ወይም እነዚህን መሠረት በማድረግ የተላለፉ ትዕዛዞችን ይጥሳል ብሎ የሚያምን ዕጩ ተወዳዳሪ በየደረጃው ባለ የገንዘብ ኢኮኖሚልማት ቢሮና ቢሮና አከላቱ እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ተጣርቶ ውሣኔ እንዲሰጥለት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ይወሠናል፡፡
2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም፡-

   ሀ/ በምዕራፍ 2 በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የግዥ ዘዴዎች ምርጫ፣

   ለ/ በአንቀጽ 18 መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሃሣብን ውድቅ ለማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ፣

   ሐ/ ግዥ ፈፃሚ አካሉ ንብረቱን ለማስወገድ በመረጠው የማስወገጃ ዘዴ፣

   መ/ በመንግስት ንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ላይ፡፡



# CHAPTER TWELVE
# COMPLAINTS THAT MAY BE LODGED WITH REGARD TO PROCEEDINGS OF PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY DISPOSAL

## 56. General

1. Without prejudice to the provisions of this chapter, a candidate shall be entitled to submit a complaint to the grievance hearing and giving decision process against an act or omission of the procuring entity in regard to a public procurement or property disposal proceeding where he believes that such an act or omission violates this proclamation or the directives. Detailed implementation shall be decided with the Bureau to be issued.

2. No complaint may be lodged in accordance with sub-article 1 of this Article in respect of the following matters:

   a) The selection of procurement method pursuant to chapter 2 of this proclamation;

   b) The decision given to the rejection of bids, proposals pursuant to Article 18 of this proclamation;

   c) The selection method of property disposal;

   d) The handling and usage of public property.

3. ግዥ ፈፃሚ አካሉ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተወዳዳሪ ጋር የግዥ ውል ከፈረመ በኋላ፣ ሂደቱን ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ ግዥ ፈፃሚ አካሉ በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አከላቱ እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ሊታዩ አይችሉም፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-

ሀ/ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግዥ ፈፃሚ አካሉ አቤቱታ ባለመቅረቡ ውል የተፈረመ ከሆነ፣

ለ/ አቤቱታ ቀርቦ ግዥ ፈፃሚ አካሉ ምላሽ የሰጠና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ አሸናፊው ከተገለፀ በኋላ ውል ለመፈረም የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በመጠናቀቁ ውል የተፈረመ ከሆነ፡፡

## 57. ለግዥ ፈፃሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. በግዥ ፈፃሚ አካሉ በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለግዥ ፈፃሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ ይሆናል።

2. እጩ ተወዳዳሪው አቤቱታውን ለአቤቱታው መሰረት የሆነውን ውሣኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በመመሪያው በሚወሰነው ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

3. Complaints against an act or omission of a procuring entity pertaining to a proceeding leading to an award may not be brought before the bodies of administration after the contract has been signed with the successful bidder.

4. The provision of sub-article 3 of this article shall apply where the following conditions are satisfied:

a) Where the contract has been signed without a complaint being filed with the procuring entity within the time limit prescribed in the directive;

b) Where the procuring entity responds to the complaint lodged and a contract is signed because of the expiration of the time limit for the signing of contract after the award without the candidate pursuing its complaint further.

## 57. Review of Complaints by the Head of Procuring Entity

1. A complaint against an act or omission by the procuring entity shall in the first instance, be submitted to the head of the procuring entity.

2. A candidate shall have to submit the complaint within days to be issue by the directive from the date he knew or should have known the circumstances giving rise to the complaint.

3. አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካሉ የግዥውን ወይም የንብረት አወጋገዱን አፈፃፀም ማገድ እና አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በመመሪያው በሚወሰነው ቀናት መሰረት ውሣኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

4. የግዥ ፈፃሚ አካሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በግዥ ፈፃሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ ውሣኔ ያልረካ እንደሆነ በግዥ ፈፃሚ አካሉ ውሣኔ ከተገለፀለት ቀን አንስቶ በመመሪያው በሚወሰነው ቀናት መሰረት በየደረጃው በሚገኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አካላቱ እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

## 58. በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

1. በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አከላት እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካከባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሲቀርብላቸው ወዲያውኑ አግባብ ላለው የግዥ ፈፃሚ አካል አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይልካል፡፡ አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንደተላከ ግዥ ፈፃሚ አካሉ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት፡፡ አቤቱታውን ለመፍታት ጊዜ አይኖርም ተብሎ ሲገመት በየደረጃው ያለ አቤቱታውን የሚያጣራ አካል በቦታው ተገኝቶ አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

3. Unless the compliant is resolved by mutual agreement, the procuring entity shall suspend the procurement or property disposal proceedings and shall, within days to be issued by the directive after submission of the compliant, issue a written decision, stating the reasons, and if, the complaint is up held, indicating the corrective measures to be taken.

4. If the procuring entity does not issue a decision within the time stated in sub-article 3 of this Article, or if the candidate is not satisfied with the decision of the head of the procuring entity the candidate is entitled to submit a complaint to the grievance hearing and giving decision process within days to be issued by the directive from the date on which the decision has been or should have been communicated to the candidate by the procuring entity.

## 58. Review of complaints by bodies of Finance and Economic Development Bureau in Different Levels

1. Upon receipt of a complaint, the bodies of finance and economic development Bureau in defferent levels as well as the city finance and economic development office shall promptly give notice of the complaint to the respective procuring entity. Such action automatically suspends further action by the procuring entity until the matter has been settled. If assumed no time to resolve the complaint, the issue concerned body has a responsibility to give decision.

2. በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አከላት እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካከባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት የዕጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ ካላደረጉ በስተቀር፣ የግዥ ፈፃሚ አካሉ ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሣኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ ወይም ከሕግ ውጪ የሆነውን የግዥ ሥርዓት እንዳይከተል ሊያደርግ ወይም ግዥ ፈፃሚ አካሉ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሥራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ ሊያስተላልፍ፣ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ውሣኔዎች በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካሉ ሥራውን እንዲያከናውን ወይም ከሕግ ውጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሣኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. The bodies of finance and economic development bureau in different levels as well as the city finance and economic development office, unless it dismisses the compliant, may prohibit the procuring entity from acting or deciding unlawfully or from following an unlawful procedure, may order the procuring entity to proceed in whole or in part an unlawful act or decision by the procuring entity other than a decision to award or conclude a contract.

3. በየደረጃው የሚገኙ የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አከላት እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካከባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት በአቤቱታው ላይ ውሣኔ ከመስጠታቸው በፊት ስለአቤቱታው ለማወቅ ፍላጐት ላላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅና፣ ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች እና ከግዥ ፈፃሚ አካሉ የቀረበውን መረጃ እና መከራከሪያ መርምሮ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

3. The bodes of finance and economic development Bureau in different levels as well as the city finance and economic development office shall, before taking a decision regarding a compliant notify interested candidates of the compliant notify interested candidate of the compliant and shall take into account information and arguments received from such candidates and form the procuring entity.

4. በየደረጃው የሚገኙ የገንዘብ ኢኮኖሚልማት ቢሮና አከላት እንዲሁም በከተማ የገንዘብና አካከባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በመመሪያው በሚወሰነው ቀናት መሰረት ለዉሳኔዉ ምክንያት የሆኑትንና የተወሰዱትን የመፍትሂ እርምጃዎች በመጥቀስ ዉሳኔን በጽሑፍ ለአቤቱታ አቅራቢውና ለግዥ ፈፃሚ አካሉ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. The bodes of finance and economic development Bureau in different levels as well as the city finance and economic development office shall issue its decision within days to be issued by the directive of receiving the compliant stating the reasons in written from for its decision and remedies granted if any for the complainer and the procuring entity.

# ምዕራፍ አስራ ሦስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 59. የመተባበር ግዴታና ኃላፊነት

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ከሚመለከታቸው አካት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡ ይህንን አዋጅ የጣሰ ወይም አፈፃፀሙን ያሰናከለ አግባብ ባለዉ የፍትሐ ብሔር ህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ሲሆን የዲሲፒሊን ግድፈትን በተመለከተ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ይጠየቃል፡፡

## 60. የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በማናቸዉም ግዥ ፈፃሚ አካል የተሾመ ወይም የተመደበ ሰዉ፣

ሀ/ በህግ መሠረት ሊከፈለዉ ከሚገባው በስተቀር የተመደበበትን ሥራ በማከናወን ማናቸዉንም ክፍያ ከተቀበለ፣

ለ/ የግዥ ፈፃሚ አካሉን የግዥ አሰራርና ንብረት አያያዝ በማጭበርበር ወይም ሌላ ሰዉ እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣

ሐ/ ህጉን የጣሰ ወይም በሌላ ማንኛዉም ሰዉ ህጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፣

መ/ በፈቃደኝነት በማናቸውም መንገድ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የፈረመ ወይም የመዘገበ ወይም ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት የሰጠ፣በፍርድ ቤት ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከብር 25,000 /ሀያ አምስት ሺ/ በማያንስ እና ከብር 35,000 /ሠላሳ አምስት ሺ/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከ10 /አስር/ ዓመት በማያንስ እና ከ15 /አስራ አምስት/ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

# CHAPTER THIRTEEN
# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 59. Duty and Responsibility to Cooperate

Any person has an obligation to cooperate with pertinent bodies for the implementation of this proclamation. Any person who violates this proclamation or influence its implementation shall be accountable by the proper civil code and for the disciplinary offence, he shall be accountable by the Amhara National Regional State civil servants proclamation.

## 60. Offences and Punishment

1. Every person appointed to or employed by a procuring entity in executing this proclamation who:

a) Receives any payment for the performance of his official duty, except as provided by law;

b) Conspires or colludes with any person to defraud the procuring entity or provides an opportunity for any person to defraud the procuring entity in regard to a public procurement and property handling;

c) Contravenes this proclamation or intentionally permits any contravention of the law;

d) Willfully makes or signs any false entry in any document or willfully makes or signs false certificate; is liable on conviction to a fine not less than Birr 25, 000.000 / Twenty five Thousand/ and not more than 35,000.00/Thirty five thousand /and to rigorous imprisonment for a term of not less than 10/ten/ years and not more than 15 /fifteen/ years if guilty is ensured with court.

2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም ከተቀጠረ ማናቸዉም የግዥ ባለሙያ በዚህ አዋጅ ይፋ እንዲሆን ከታዘዘዉ አይነት መረጃ በስተቀር፣

ሀ/ ግዥዉን በማስፈፀም እረገድ ባለዉ ስልጣን ወይም ኃላፊነት ምክንያት ያወቀዉን የሌላሰዉ ማናቸዉም መረጃ ለማናቸዉም ሌላ ሰዉ ወይም የዚህ ሰዉ ወኪል አሳልፎ የሰጠ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ግዥን በማከናወን እረገድ ያለዉን ስልጣን ለማስፈፀም ወይም የሥራ ግዴታዉን ለመወጣት እንዲያስችል ግዥዉን በሚፈፅመዉ መስሪያ ቤት ዘንድ የሚገኘዉን ማናቸዉንም መረጃ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ሐ/ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10,000 /አስር ሺ/ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ2 /ከሁለት/ ዓመት በማያንስና ከ5 /አምስት/ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ለማዋል ግዥዉን በሚፈፅመዉ መስሪያ ቤት የተቀጠረ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ፣

ሀ/ በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የገንዘብን ወይም ሌላ አይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያዉ ወይም ለስጦታዉ ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ ወይም

2. A procurement officer employed in carrying the provisions of this proclamation, except such information is required by this proclamation to be official, who:

a) Discloses to any person or that person's representative any matter in respect of an other person that may in the exercise of the procurement officer's powers or the performance of the procurement officer's duties come to the procurement officer's knowledge;

b) Permits any other person to have access to records in the possession or custody of the procuring entity ,except in the exercise of the procurement officer's powers or the performance of the procurement officer's duties under this proclamation or by order of a court;

c) Commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than Birr 10,000.00 /ten thousand/ and imprisonment for a term of not less than 2years and not more than 5 years.

3. Every person appointed to or employed by a procuring entity in carrying out the provisions of this proclamation who:

a) Directly or indirectly asks for or receives in connection with any of his duties a payment or gift whether pecuniary or otherwise or promise or security for that payment or reward; or

ለ/ በግዥ ተግባር ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም የተሰጠዉ ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም ማድረግ የሚገባዉን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግዥ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ዉል የገባ ወይም በሚገባዉ ዉል ዉስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣ እንደሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000/ሀምሳ ሺ/ የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10/አስር/ ዓመት በማያንስ ከ20/ሀያ/ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

4. ማንኛዉም ሰዉ በመንግስት ግዥ ላይ ለተሾመ ወይም ለተመደበ ሰው፣

ሀ/ የቀረበለትን ዉሳኔ በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉዳይ ወይም በስራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀርብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠዉን ዉሳኔ ወይም የሚወሰደዉን እርምጃ ለማዛባት ወይም

ለ/ በመንግስት ግዥ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፀም ወይም ድርጊቱ ይፈፀም ዘንድ እንዲረዳ ወይም እንዲተባበር ወይም ለድርጊቱ መፈፀም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንዲስማማ፣ እንዲመሳጠር ወይም እንዲፈቅድ ለማድረግ በማሰብ ጉቦ ለመስጠት ቃል ከገባለት፣ከቀረበለት ወይም ከሰጠዉ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ ከብር 50,000/ሀምሳ ሺ/ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10/አስር/ ዓመት የማያንስና ከ20/ሀያ/ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

b) Enters into or acquiesces in an agreement to do or to obstinate from doing, permit conceal, or connive at any act or thing whereby the procurement is or may be defrauded or which is contrary to the provisions of this proclamation or to the proper execution of the procurement officer's duty; commits an offence and is liable on conviction to a fine of not more than 50,000.00/fifty thousand/Birr and to imprisonment for a term of not less than 10 years and not more than 20 years.

4. Any person who promises, offers or gives any bribe to any person appointed to or employed in any procuring entity with intent:

a) To influence the decision or action of that person on any question or matter that is pending, or may be brought before him in his official capacity; or

b) To influence that person to commit, or aid or abet in committing any fraud on the procurement, or to connive at, collide in or allow or permit any opportunity for the commission of any such fraud; is guilty of an offence and liable on conviction to a fine of not less than Birr 50,000.00 / Fifty Thousand / and to a rigorous imprisonment for a term of not less than 10 years and not more than 20 years unless higher punishment is prescribed on the penal code this will have effect otherwise.

5. ማንኛዉም እጩ ተወዳዳሪ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ የሀሰት ማስረጃ ካቀረበ ወይንም መግለፅ የነበረበትን መረጃ ከደበቀ ወይም ከሌላ እጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሣጠር የሀሰት ዉድድር ማድረጉ ከታወቀ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ ከብር 20,000/ሀያ ሺ/ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ5 /አምስት/ ዓመት የማያንስና ከ10 /አስር/ ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## 61. ስለ ግል ግል

በግዥ ፈፃሚ አካሉ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ በቅድሚያ ጉዳዩ የሚታየዉ ሁለቱ ወገኖች በሚመርጧቸዉ ገላጋዮች አማካኝነት ይሆናል፡፡

## 62. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም እንዳስፈላጊነቱ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቢሮዉ ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጣዉን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 63. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ በሂደት ላይ ያሉና ውል የተያዘባቸው ግዢዎች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 135/1998 ዓ.ም እና እሱን ተከትለዉ ቢሮው ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ተፈፃሚ እየሆኑ ይቆያሉ።

5. Any candidate who, with the intention of deriving unlawful advantage, presents falsified documentary evidence or conceals any evidence which he should have disclosed or connives at an act of take competition shall upon conviction be punishable with fine not less than 20,000/Twenty Thousand / Birr and with rigorous imprisonment of not less than 5 years and not more than 10 years.

## 61. Arbitration

Where a disagreement arises between the procuring entity and the candidate, such issue shall firstly be dealt by arbitrators to be chosen by the two parties.

## 62. Power to Issue Regulation and Directives

1. The council of Regional Government may, where necessary, issue regulation for the implementation of this proclamation.
2. The Bureau may issue directives to help for the implementation of this proclamation and regulation to be issued pursuant to this proclamation.

## 63. Transitory Provision

Procurements that are being undertaken and to which contracts have been made until to the issuance of this proclamation with the Regional Zikre-Hig gazette, shall be executed by ANRS proclamation No . 135/2006 and the directives issued by the Bureau.

## 64. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. የአማራ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 135/1998 ዓ.ም ይህ አዋጅ በዝክረ ህግ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተሽሯል፡፡

2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 65. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባሕር ዳር**

**ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም**

**አያሌው ጎበዜ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት**

## 64. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Amhara National Regional State public procurement procedure determining proclamation No.135/2006 is repealed till the date of issuance of this Proclamation by the Zikre-Hig Gazettee.

2. No law, regulations, directives or practices inconsistent with this proclamation shall have effect with respect to matters provided for in this proclamation.

## 65. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazettee of the Regional State.

**Done at Bahir Dar,**

**This 5th day of July, 2011.**

**Ayalew Gobezie**

**President of the Amhara National Regional State**